ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ

84ኛ ዓመት ቁጥር 043 ጥቅምት 13 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# አዲሱ የገንዘብ ማሻሻያ ምን አስገኘ?

**ዳግማዊት አበበ**


**ዜና ትንታኔ**

የፌዴራል መንግሥት ሀገሪቷ የነበረችበትን የኢኮኖሚ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ማሻሻያው ከፋይናንስና ምንዛሬ፣ ከምርታማነትና ከሥራ እድል ፈጠራ አንፃር መሠረታዊ ለውጦችን ይዞ መምጣቱን የገንዘብ ሚኒስቴር ማስታወቁ አይዘነጋም።

ማሻሻያዎቹ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚታዩትን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ለመቅረፍ አቅም ያላቸው ቢሆንም ጠንካራ ሥራን የሚጠይቁ መሆናቸው አያጠያይቅም። ማሻሻያውን መሠረት አድርገው ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም እና የዓለም ባንክ እስከ ነሀሴ ወር 2016 ዓ.ም ብቻ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ማቅረባቸውን ብሔራዊ ባንክ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

በገንዘብ ማሻሻያው ኢኮኖሚውን ወደሚፈለገው ደረጃ

**አዲሱ የገንዘብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




# ካፍ የኢትዮጵያን ጥያቄ እንዲያፀድቅ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ጥሪ አቀረቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ኢትዮጵያ ያቀረበችውን የአፍሪካ ዋንጫን የማስተናገድ ጥያቄ ተቀብሎ እንዲያጸድቅ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ጥሪ አቀረቡ።

46ኛው የካፍ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ትናንትና በአዲስ አበባ ስካይላይት ሆቴል ሲጀመር የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንት ታዬ፤ ካፍ የኢትዮጵያን የ2029 የአፍሪካ ዋንጫ የማስተናገድ ጥያቄ እንዲቀበልና እንዲያጸድቅ ጠይቀዋል።

"አፍሪካውያን ቤታችሁ ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ እንኳን ደህና መጣችሁ" ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ እግር ኳስ ትልቅ ዐሻራ እንዳላትና ካፍን ከ67 ዓመት በፊት ከመሠረቱ ሀገራት አንዷ እንደነበረች አስታውሰዋል።

የካፍ ፕሬዚዳንት የነበሩት ይድነቃቸው ተሰማ የአፍሪካ እግር ኳስ በዓለም መድረክ የሚገባውን ቦታ እንዲያገኝ የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እግር ኳስ ወዳጆች ሀገር ናት ብለዋል።

**ካፍ የኢትዮጵያን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



# "ሰውን መጉዳት በማቆም ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዕድል መስጠት ይገባል"

**- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ**

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ሰውን መጉዳትና እግዚአብሔርን መዳፈር በማቆም ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እድል መስጠት ይገባል ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፓትሪያሪክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያሪክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔን ትናንት አስጀምረዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የቅዱስ

**"ሰውን መጉዳት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# የቢዝነስ ጉባዔው በኢትዮጵያና ኦስትሪያ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ያጠናክራል



**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የቢዝነስ ጉባዔው በኢትዮጵያና ኦስትሪያ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት እንደሚያጠናክር የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሪታ ሰዋሰው ገልጸዋል። የ60ኛ ዓመታት የዲፕሎማሲ አጋርነት አስመልክቶ የኢትዮ- ኦስትሪያ የቢዝነስ ጉባዔ በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በጉባዔው ላይ ንግግር ያደረጉት የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሪታ ሰዋሰው፣ የቢዝነስ ጉባዔው የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት

**የቢዝነስ ጉባዔው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**









# አሳታፊው የሀገራዊ ምክክር ሒደት

**ውብሸት ሰንደቁ**

ባለፈው ሳምንት የሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማን ጨምሮ በሌሎች ሦስት ማዕከላት የሀገራዊ ምክክር አጀንዳ ልየታ መድረክ ሲከናወን ቆይቷል።የአጀንዳ ልየታው ተጠናቅቆ ወደ ባለድርሻ አካላት ምክክር ተሸጋግሯል።

ሂደቱን በማስተባበር እያካሄደ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የማይናወጡ መርሆዎቼ ናቸው ብሎ ካስቀመጣቸው ምሶሶዎች ውስጥ አንዱና የመጀመሪያ ረድፍ ላይ ያለው “አካታችነት” ነው።አካታችነት በምክክሩ ውስጥ ባለ የአጀንዳ እና የሃሳብ ማዋጣት ተሳትፎ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲሳተፍ የሚያደርግበት መንገድ መሆኑን የሚዳስስ ጽንሰሃሳብ ሆኖ እናገኘዋለን።


በዚህ አካሄድ ተጠቃሚ ሆነው ውክልና ተሰጥቷቸው በምክክሩ ላይ ሲሳተፉ ካገኘናቸው ውስጥ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ይገኙበታል።

ሰዎች በሚሠሩት ሥራ ወይም በሌላ አንዳች ምክንያት አልያም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ጎሳዎች በመሆናቸው በአንዳንድ አካባቢዎች መገለል ይደርስባቸዋል።እነዚህ ዜጎች ኢትዮጵያዊ እንደመሆናቸው መጠን የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅ፤ ለሀገር ያላቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረታ እንዲሁም ዕኩልነታቸውን በግልፅ የሚያውጅ አጀንዳ ማንሳትና መወያየት ያስፈልጋል።በመሆኑም በሀገራዊ ምክክሩ ተገቢው ቦታና ውክልና ተሰጥቷቸው እየተወያዩ ይገኛል።

በምክክሩ በተለያየ ምክንያት የተገለሉ ማኅበረሰቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትና ዕኩልነት ፋይዳ ያላቸው አጀንዳዎችን መለየታቸውንም በሶማሌ ክልል ሀገራዊ ምክክር የተገለሉ ማኅበረሰቦች ተወካዮች ለኢፕድ ተናግረዋል።

በሶማሌ ክልል ሀገራዊ ምክክር የአጀንዳ ልየታ የተሳተፈው አቶ አብዱአዚዝ ዩሱፍ፤ በክልሉ በአካል ጉዳተኝነት እና በጎሳ ምክንያት የተገለሉ ሰዎች አሉ ይላል።

በበርካታ የክልሉ አካባቢዎች ማኅበረሰቡ ባያገልላቸው እንኳን ራሳቸውን የሚያገልሉ ጥቂት ሰዎች እንዳሉ በመጥቀስ፤ በትንሹም ቢሆን የመገለል ችግር ከታየ በምክክር ሊፈታ እንደሚገባው ነው የሚናገረው።



አቶ አብዱአዚዝ ዩሱፍ



ወጣት ኢክራም ኢብሳ



አቶ ባሪ ቀረኒ

ኢትዮጵያ የትኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል ዕኩል የምታይ ሀገር መሆን ይኖርባታል የሚል ዕምነት እንዳለውም ወጣት አብዱአዚዝ ይጠቅሳል።

በምክክሩ ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና ዕኩልነት ፋይዳ ያላቸው አጀንዳዎችን በመለየት መሰል ችግሮች በምክክር ተፈትተው ኢትዮጵያ ሰላማዊ እና ለሁሉም ዕኩል የምትመች ሀገር ሆና የማየት ተስፋ እንዳለው ይናገራል።

የተለዩ አጀንዳዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ውይይት ተደርጎባቸው ወደ ተግባር ይገባሉ የሚል ዕምነት እንዳለው ገልጾ፤ ጎን ለጎን ለማኅበረሰቡ ሁሉም ሰው ዕኩል ስለመሆኑ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይገባል ይላል።

የማግለል ትንሽ ትልቅ የለውም የምትለው ደግሞ ከሽኒሌ ወረዳ የምክክሩ ተሳታፊ የነበረችው ወጣት ኢክራም ኢብሳ ናት።

በአንዳንድ ቦታዎች ማግለል ባይኖር እንኳን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ጎሳዎች ራሳቸውን የሚያገሉበት ሁኔታ እንዳለ የምትገልጸው ወጣት ኢክራም፤ በየትኛውም መንገድ ቢሆን ኢትዮጵያ የሁላችን ሀገር መሆኗን በመገንዘብ ሁሉንም ስህተቶች በምክክር ማረም ይገባል ትላለች።

በምክክሩ የተገለሉትን ዜጎችን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡና ዕኩልነትን የሚያሰፍኑ አጀንዳዎች መለየታቸውን ነው የጠቆመችው።

በተለዩ አጀንዳዎች ላይ የሚደረግ የባለድርሻ አካላት ውይይት አስፈላጊ መሆኑን አንስተው፤ በአጠቃላይ የሀገራዊ ምክክሩ ለሀገር የሚበጅ ውጤት ያመጣል የሚል ተስፋ አለኝ ስትል ትገልጻለች።

ከጀረር ዞን ዮአሌ ወረዳ የተገኙት የምክክሩ ተሳታፊ አቶ ባሪ ቀረኒ በበኩላቸው፤ ምክክር ለአንድ ሀገር ቀጣይ ጉዞ ወሳኝ መሆኑን ያነሳሉ።

የተገለሉ ማኅበረሰቦች ከሕዝቡ ጋር በዕኩልነት እንዲኖሩ ማስቻል ያስፈልጋል የሚሉት አቶ ባሪ፤ ጉዳዩን አጀንዳ አድርጎ በመወያየት እና የሕዝቡን ግንዛቤ በማሳደግ መሰል ችግሮችን መፍታት እንደሚያስፈልግ ያብራራሉ።

ሀገራት ችግሮቻቸውን በምክክር ሲፈቱ ያለ ተጨማሪ ጉዳት ምቹ ከባቢን መፍጠር እንደሚችሉ አስገንዝበው፤ ምክክሩ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ዕድልን ይዞ እንደመጣ ዕምነታቸው መሆኑን ነው ያመላከቱት።

# በጤና ለመኖር አስቀድሞ መመርመር

**ማህሌት ብዙነህ**

**ዜና ሐተታ**

እንደካንሰር፣ ስኳር፣ ደም ብዛትና ሌሎችም ቀድሞ ከተደረሰባቸውና ምርመራ ከተደረገ ሊስተካከሉ የሚችሉ በሽታዎች መሆናቸውን የጤና ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ደግሞ የጤና እክል ካላጋጠመው በቀር አስቀድሞ ከጤና ባለሙያዎች ጋር የመገናኘትና ወደ ሕክምና ማዕከላት ሄዶ የመመርመር ልምዱ አናሳ ነው።በዚህም አንዳንድ በሽታዎች በጊዜ ሳይደረስባቸው ስር በመስደድ ለከፍተኛ ህመምና ወጪንም ሊያስወጣ ይችላል።

ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ እንደሚለው ብሂሉ በማንኛውም ወቅት ከሚከሰት የከፋ ህመም ለመጠበቅ በትንሹ በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ የጤና ምርመራ እንደሚገባ የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ።

ቀድሞ መከላከል የሚቻሉ የጤና እክሎችን በምርመራ በማወቅ እስከ የሕይወት ህልፈት የሚያደርሱ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያችል ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ይጠቁማሉ። ታዲያ የጤና ቅርመ ምርመራ ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? በሚያስገኘው ጥቅሞች ዙሪያ ምን አይነት ግንዛቤ ያስፈልጋል በሚሉ ጉዳዮች ላይ ኢፕድ የጤና ባለሙያዎችን አነጋግሯል።

የጤና ባለሙያ የሆኑት ሞገስ አብርሃ (ዶ/ር) እንሚያስረዱት፤ በሀገራችን ያለው አነስተኛ ግንዛቤ ምክንያት በአብዛኛው ማህበረሰብ ወደ ጤና ማዕከላት በማቅናት የመመርመርና የማማከር ባህል ዝቅተኛ ነው።

ወደ ህክምና ተቋማት የሚመጡት በሽታው ከፍ ያለ ጉዳት ሲደርስባቸው ብቻ ነው።ስለጤናው ሁኔታ ባለማወቅ እና ቅድመ ምርመራ ባለ ማድረግ ሳቢያም ለከፍተኛ ህመም ብሎም ሞት ይዳረጋል ይላሉ።

ይህንን ለመከላከልም በሽታዎች ከመከሰቱ በፊት



በምናደርጋቸው ምርመራዎች እንደ ልብ፣ ስኳር፣ ደምግፊት፣ ኩላሊትና ካንሰር የመሳሰሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቀድሞ መከላከል የሚቻልበት አቅም ስላለ ምርመራ ወሳኝ መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር ሞገስ እንደሚሉት፤ ቅድመ ምርመራ ማድረግ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች በተጨማሪ በዘር እና በእድሜ መግፋት የሚከሰቱ በሽታዎች የተጋላጭት ስጋት ለመለየትና በቅድመ ጥንቃቄ ለመከላከል ያግዛል።

የደም፣ የሽንት፣ የውስጥ ደቄ፣ የሲቲ ስካንና አጠቃላይ ምርመራዎች የሕመም ምልክቶች በብዛትና ሳይታዩ አስቀድሞ በሽታው እንዲለይና ሕክምና እንዲሰጥ ለማድረግ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው፤ በበሽታው ሊያደርስ የሚችለውን የከፋ ጉዳት በከፍተኛ መጠን ለመቀነስ ሁሉም ዜጋ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጤና ተቋመ በመሄድ መመርመር እንደሚገባው ይመክራሉ።

ለአብነትም የስኳር በሽታ የሕመም ስሜት የሚኖረው አምስት ዓመት በሰውነት ውስጥ ከቆየ በኋላ መሆኑን አንስተው፤ የደም ግፊት በሽታ ደግሞ ምንም አይነት ምልክት የማያሣይ መሆኑን ይገልጻሉ። በመሆኑም ማንኛውም ሰው ተመርምሮ ካላረጋገጠ በቀር በሽታ የለብኝም ማለት አይችልም ብለዋል።

እየጨመረ የመጣውን የጡት ካንሰር፣ የማህጸን በር ካንሰር፣ የአንጀት ካንሰር የመሳሰሉት በሽታዎች ጨምሮ የትኛውንም በሽታ ቀድሞ በመመርመር በሰውነት ውስጥ ከመሰራጨቱ በፊት ማስቆም ይቻላል ይላሉ።

ቢያንስ በዓመት አንዴ አጠቃላይ የጤና ምርመራ በማድረግ በማንኛውም ሰዓት ከሚደርስ የከፋ የጤና እክልና ለሕክምና ከሚወጣ ወጪ መዳን እንደሚቻል ዶክተር ሞገስ ያመላክታሉ።

የረዳት ሄልዝ ኬር ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ምስጋና ሰለሞን በበኩላቸው፤ በአብዛኛው ሰው በጠና ካልታመመ በቀር ወደ ህክምና ተቋማት የመሄድ ባህል ዝቅተኛ መሆኑን ያነሳሉ።

ቀድሞ መመርመር እና ቀድሞ ስለበሽታዎች ማሰብ እንደሟርትና በሽታን እንደመጥራት ይቆጠራል።ይህንን ባህል ለመቀየር እና ግንዛቤ ለመፍጠርም ብዙ መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ።

ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ቀድሞ መከላከል እንዲሁም ከፍ ያለ ጉዳት ሳያስከትሉ ማወቅ ዋነኛው በሽታዎቹን ለመቆጣጠር የሚያስችል መንገድ መሆኑን ያስረዳሉ።

በመሆኑም ቅድመ ምርመራን በስድስት ወር ወይም በዓመት እንደየ እድሜና ፆታ ልዩነት የተለዩ የቅድመ ምርመራዎችን በማድረግ እራስን ማወቅ ተገቢ መሆኑን ይመክራሉ። ከዚህ ባለፈ ምርመራው ለወደፊት ለየትኛው በሽታ የመጋለጥ እድል እንዳለን ለማወቅና ለመጠንቀቅ ያስችላል ሲሉ ይናገራሉ።

የሰው ልጅን በብዛት እያጠቁ የሚገኙ በሽታዎች አስቀድሞ መከላከል የሚቻሉ ናቸው ያሉት ወይዘሮ ምስጋና፤ በመሆኑም የጤና ምርመራ ማድረግና ጤናማ የሆነ የአኗኗር መንገድን ለመከተል ያለውን ሚና በመገንዘብ ከስር ከስር የጤና ሁኔታን መከታተል እንደሚገባ ምክረ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

# ከወንጀል ምዝገባ እስከ ውሳኔ ያለውን ሂደት ግልጽ የሚያደርግ አሠራር ሊዘረጋ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ፍትህ ሚኒስቴር ከወንጀል ምዝገባ እስከ ውሳኔ ያለውን ሂደት በግልጽ ማወቅ የሚቻልበት የተቀናጀ የወንጀል የመረጃ ሥርዓት ሊዘረጋ መሆኑን አሳወቀ።

የፍትሕ ሚኒስቴርና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የተቀናጀ የወንጀል የመረጃ ሥርዓትን ለማልማት የሚያስችል ስምምነት ትናንትና ተፈራርመዋል። የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነብርሃን (ዶ/ር) እና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) ናቸው።

የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነብርሃን (ዶ/ር)፤ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 12 የመንግሥት አሠራር ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት እንደሚደነግግ እንዲሁም፤ መንግሥት ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ፍትህ ሚኒስቴርም የተሰጡትን ሃላፊነቶች ለመወጣት የወንጀል ምርመራ፣ ክርክር፣ ክስና ማስቀጣትን በተመለከተ ሰፋፊ ሃላፊነቶች እንዳሉበት አንስተዋል።

በተግባሮቹ ውስጥ ፌዴራል ፖሊስ፣ ፍትህ ሚኒስቴር ተቀናጅተው ከሚሠሯቸው ሥራዎች መካከል ዋነኛው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር መሆኑን ጠቁመዋል።

የወንጀል መዝገብ መረጃ ሥርዓት ወቅቱን የዋጀ፣ ዘመናዊ፣ ግልጽ፣ ተጠያቂነትን ያሰፈነ፣ ቀልጣፋ ደህንነቱ የተረጋገጠ ሥርዓት ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ከኢንስቲትዩቱ ጋር ለአንድ ዓመት ያህል ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን አስታውሰዋል።

በተደረገው ስምምነት መሠረት ማስረጃን መሠረት በማድረግ በተለየ መልኩ ሰው ሰራሽ አስተውሎትን (አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን) በመጠቀም እያንዳንዱን አገልግሎት ግልጽ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን የሚያስችል ሥራ መጀመሩን አስረድተዋል።

ከወንጀል ምዝገባ እስከ ውሳኔ ያለውን ሂደት በግልጽ ማወቅ የሚቻልበት ሥርዓት በመዘርጋት በፍትህ ሥርዓቱ ጉልህ ሚና የሚጫወት ተግባር ሊሆን የሚችል መሠረት መጣሉን ጠቁመዋል።

ስምምነቱ በተለይም የባለሙያ እንግልትን ከመቀነስ፣ የዐቃቤ ሕግና የፖሊስ የወንጀል ውስጥ ያለውን ሂደት በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ የሚያስችል መሆኑ ተናግረዋል።ስምምነቱ የወንጀል የመረጃ ሥርዓትን በማዘመን ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልጸዋል።

የአርተፊሽያል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሥርዓቱ ህብረተሰቡ ቤቱ ሆኖ ቴክኖሎጂን መጠቀም የሚረዳውና ከፍትህ አካላት ጋር በመገናኘት የፍትህ ሥርዓቱን ግልጽነት ለማስፈን የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

ህብረተሰቡ የሚከታተላቸው ጉዳዮች የት እንደደረደሱ የሚከታተልበት በሰው ሠራሽ አስተውሎት የተደገፈ መሆኑንም አመላክተዋል።ደንበኞች በተለያዩ ቋንቋዎች በመጠቀም የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችላቸው መሆኑንም አመልክተዋል።

አሠራሩ ሲተገበር ሕዝቡ በፍርድ ቤት ላይ እምነት እንዲያሳድር በማድረግም የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም ተናግረዋል።ከፌዴራል ፖሊስ እና ክክልል የፍትህ አካት ጋር የሰመረ ግንኙነት በመፍጠር መረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ቢሆንም ከተያዘው ጊዜ ባነሰና በተገባው የጥራት ውል መሠረት አጠናቅቆ ለማስረከብ ትኩረት ይሰጣል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ 84 ሚሊዮ ብር የተያዘለት ሲሆን፤ ሥራውን አጠናቅቆ ለማስረከብ አንድ ዓመት እንደሚፈጅ ተጠቁሟል።

# "አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ እንደ ሀገር የተያዘውን እቅድ ከግብ ለማድረስ ያግዛል"

- ግርማ አመንቴ(ዶ/ር)
የግብርና ሚኒስትር

**ዳግማዊት አበበ**



ቢሾፍቱ፡- አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ እንደ ሀገር የተያዘውን እቅድ ከግብ ለማድረስ ያግዛል ሲሉ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመቴ (ዶ/ር) ገለጹ።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አዲሱን የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ትናንት ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልል ግብርና ኃላፊዎች ሲያስተዋውቅ እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም የነበረው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ከ20 ዓመት በፊት የወጣና አሁን ከሚሠሩ የግብርናው ዘርፍ ሥራዎች ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም።ይህን መነሻ በማድረግም አዲስ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል።

አዲሱ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲም እንደ ሀገር የተያዘውን እቅድ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ መሆኑን ገልጸው፤ፖሊሲውን የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ፖሊሲው ውስጥ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮችን አውቆ እንዲተገብር ያደርገዋል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ፖሊሲው አሁን የግብርናው ዘርፍ ያለበትን ደረጃ ብቻ የሚያይ ሳይሆን ኢትዮጵያ ወደፊት ልትደርስበት ካሰበችው ቦታ የሚያደርስ ነው።በፖሊሲው ዙሪያም ግንዛቤ ተፈጥሮ ቶሎ ወደ ተግባር መግባት ያስፈልጋል።

ሚኒስትሩ፤ በፖሊሲው ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ የግብርና ፋይናንስ አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ያለውን የፋይናንስ ሥርዓት መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ባንክ ማቋቋም የሚቻልበትን ሁኔታ የሚያመቻች ፖሊሲ መሆኑን ተናግረዋል።

የመሬትና ተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ የመሬት ሀብት አሲዞ ብድር ማግኘት እንደሚቻል በፖሊስው መቀመጡን የጠቆሙት ግርማ ( ዶ/ር)፤ ለዚህ የሚሆን ተጨማሪ መመሪያና ደንብ እንደሚያስፈልግ አንስተዋል።

የግብርናው ዘርፍ ገጠሩን ህብረተሰብ ለማሻገር ወሳኝ ነው ያሉት ሚኒስትሩ ፤ ፖሊሲው የግብርናና ገጠር ልማት የተባለው ለዚህም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ፖሊሲውን የማስተዋወቅ ሥራው በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች እስከ ዞን እና ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የሚሠራ መሆኑን አመልክተው፤ የማስተዋወቅ ሥራውንም ሁሉም በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሚኒስትሩ በመድረኩ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተሠሩ ሥራዎችን በተመለከተ እንደገለፁት፤ ከግብርና የወጪ ንግድ በሩብ ዓመቱ 796 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል። ከቡና የወጪ ንግድ ብቻ 519 ሚሊዮን ዶላይ ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል ።

የሌማት ትሩፋት ንቅናቄው ባለፉት አራት ዓመታት ሲተገበር የነበረበት አካሄድን በማሻሻል በዘንድሮ ሩብ ዓመት 20 ሚሊዮን የአንድ ቀን ጫጩት ማሰራጨት ተችሏል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሥራው ሲጀመር በዓመት ይሰራጭ የነበረው የአንድ ቀን ጫጩት 26 ሚሊዮን ብቻ ነበር ብለዋል። በዚህ ዓመትም 150 ሚሊዮን የአንድ ቀን ጫጩት ለማሰራጨት መታቀዱን ጠቁመዋል።

ሀገሪቱ የያዘችውን የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለማሳካትና የኑሮ ውድነት ለማቃለል ዘንድሮ ምርትን በብዛትና በጥራት ወደ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በግብዓት አቅርቦት ረገድ የተሻለ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ ያለፈው ዓመት ተሞክሮ በመውሰድ የማዳበሪያ ግዢው ቅድሚያ እንዲፈጸም እየተደረገና ማዳበሪያ በመጓጓዝ ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

በ2017 የምርት ዘመን 24 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለማቅረብ መታቀዱን የገለፁት ሚኒስትሩ ፤የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግዱ እንዲቀንስ ማድረጉን ተናግረዋል።

# የምርጥ ተጽእኖ ፈጣሪዎች ሽልማት በሥራቸው አርዓያ የሆኑ ግለሰቦችን ለማበረታታት ያግዛል

## - ለሁለት አሸናፊዎች 20 ሚሊዮን ብር ሽልማት ይበረከታል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የምርጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ሥራዎች ሽልማትና የእውቅና መርሀ-ግብር በሥራቸው ለሌሎች አርዓያ የሆኑ ግለሰቦችን ለሚያበረታታት እንደሚያግዝ ተመላከተ። ለሁለት አሸናፊዎች በአጠቃላይ 20 ሚሊዮን ብር ሽልማት እንደሚበረከት ተጠቁሟል።

የምርጥ ተጽእኖ ፈጣሪ ሥራዎች ሽልማትና እውቅና መርሀ-ግብር ታህሳስ 17 ቀን 2017 ዓ.ም እንደሚካሄድ ታውቋል። የመርሀ-ግብሩ አዘጋጅ የአንቴክስ ጨርቃጨርቅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፕሬዚዳንት ሚስተር አንጉስ ቺን እንዳስታወቁት፤ ድርጅታቸው ለሌሎች አርዓያ የሚሆኑ ግለሰቦችንና ተቋማትን ለመሸለም አቅዷል።



ሁለት አሸናፊዎች እያንዳንዳቸው 10 ሚሊዮን ብር ሽልማት ይበረከትላቸዋል

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ላደረጉ እና በሕዝቡ መካከል ሰላማዊ አብሮነትን ለማጎልበት ለሚተጉ እንዲሁም በሥራቸውም ውጤታማ ሆነው ለሌሎች አርዓያ መሆን ለቻሉ ግለሰቦችና እና ድርጅቶች የማበረታቻ ዕውቅናና ሽልማት እንደሚሰጥ አመላክተዋል።

ሽልማቱ በሁለት ዘርፎች የሚካሄድ መሆኑን ጠቁመው፤ በኢኮኖሚ ሽልማት ዘርፍ ከትንሽ ተነስቶ በራሱ ጥረት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ የቻለ፣ ለብዙዎች የሥራ ዕድል የከፈተ፣ ሕዝብና ሀገርን ለመጥቀም የሚሠራና ካፈራው ሀብት ላይ ማህበራዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ ኢትዮጵያዊ ዕጩ ሆኖ መቅረብ እንደሚችል አስታውቀዋል።

በተጨማሪ የሰላም ሽልማት ዘርፍ ደግሞ በአናኗሩ ሰላምን ከፍ የሚያደርግ፣ ዋጋ ከፍሎ በህብረተሰብ መካከል እርቅን ለማውረድ የሠራ፣ ይቅርታን እየኖረ ይቅርታን የሰበከ፣ የፆታ አኩልነትን ያበሰረና ፆታዊ ጥቃትን የሚፀየፍ የእጩ ዝርዝር ውስጥ መካከት እንደሚችል ጠቁመዋል።

የሽልማት መርሃ-ግብሩ ታህሳሰ 17 ቀን 2017 ዓ.ም በአፍሪካ ሕብረት የስብሰባ አዳራሽ ከፍተኛ የመንግሥት አካላትና የክብር እንግዶች በተገኙበት እንደሚካሄድ አመላክተዋል። ለሁለት አሸናፊዎች ለእያንዳንዳቸው 10 ሚሊዮን ብር ሽልማትና የእውቅና ዋንጫ እንደሚበረከትላቸውም ገልጸዋል።

በውድድሩ መሳተፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ራሳቸው ወይም ጠቋሚዎች ከጥቅምት 11 ቀን ጀምሮ ለቀጣይ 15 ቀናት በቴሌግራም ቻናል @ Biwprize ወይም በኢሜይል አድራሻ biwsprize@ gmail.com መመዝገብና ጥቆማ መስጠት የሚቻል መሆኑ አስታውቀዋል።

አንቴክሰ ጨርቃጨርቅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዳማ ኢንዱስትሪያል ፓርክ የተለያዩ አላባሳትን አምርቶ ለውጭ ገበያ እያቀረበ ሲሆን፤ ለአራት ሺህ 500 ሠራተኞች የሥራ ዕድል የፈጠረ ኩባንያ መሆኑ ተጠቁሟል።

ድርጅቱ በቀጣይም 10 ሺህ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ ጉዳዮች የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት እንደሚሠራ ተመላክቷል። የምርጥ ተፅእኖ ፈጣሪ ሥራዎች የሽልማት መርሀ-ግብርም በየዓመቱ ለተከታታይ ሶስት ዓመታት እንደሚቀጥል ተገልጿል።

# አዲሱ የገንዘብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለማድረስ የሚረዱ ምን አይነት ሥራዎች ተከናውነዋል፤ ምንስ ውጤት ተገኝቷል? በግብርና፣ በማዕድን፣ በቱሪዝምና በተለያዩ ዘርፎች የተደረጉ ማሻሻያዎች የኢኮኖሚ ስብራቱን ለማሻሻል ምን አይነት አቅም ፈጥረዋል በሚሉ ጉዳዮች ላይ ምሁራንና የዘርፉ ኃላፊዎች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን በተመለከተ በቅርቡ በሰጡት ማብራሪያ እንዳነሱት፤ ከሀገራዊ ለውጡ በፊት የነበረው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ኢትዮጵያን ለውጭ ምንዛሬ እጥረትና ለከፍተኛ የብድር ጫና የዳረገ እንዲሁም የግል ሴክተሩን ከብድር አቅርቦት ያገለለ ነበር።

በቀድሞ ጊዜ የነበረው ኢኮኖሚ አካሄድ በዋናነት የመንግሥት ኢንቨስትመንትን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የፋይናንስ አቅርቦቱ ጤናማ እንዳልነበረ አንስተው፤ መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም በመተግበር የኢኮኖሚ ስብራትን ለመጠገን የሚያስችሉ ርምጃዎችን መውሰዱን ይገልጻሉ።

ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግም ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትግበራ የገቢ አስተዳደርና አሰባሰብ፣ የገንዘብ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ አስተዳደርን ጨምሮ ሁሉንም ዘርፎች በማስተሳሰር የሚተገበር መሆኑን ጠቁመው፤ የውጭ ምንዛሪ ችግርን በዘላቂነት የሚፈታ ቁልፍ ውሳኔ መሆኑንም ነው ያብራሩት።

በዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይኤምኤፍ) ትንበያ ብቻ በቀጣይ አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ ስምንት በመቶ ያድጋል ይላሉ። በዚህም ሪፎርሙ በገቢ ማሰባሰብ አቅም የሚፈጥር፣ የውጭ ምንዛሬ ክምችት የሚጨምር፣ ኤክስፖርትና ኢንቨስትመንትን ትርጉም ባለው መልኩ የሚለውጥ እንዲሁም የኢኮኖሚ ፍትሃዊነትን የሚያሰፍን እንደሆነ ያመላክታሉ።

ብሔራዊ ባንክ ካደረጋቸው ሪፎርሞች መካከል የውጭ ምንዛሬ ተመኑ በገበያ መወሰኑ ሕገ ወጥነትና ብልሹ አሠራርን በመቅረፍ ኤክስፖርትና ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ያስረዳሉ።

በዚህም የምንዛሬ ተመኑ ወደ ገበያ መር መለወጡ በሸቀጦች ዋጋ ላይ ጭማሪ ሊፈጥር እንደማይገባ ገልጸው፤ ሪፎርሙን ተከትሎ ሕገ-ወጥነትና አሉታዊ ጫና የሚፈጥሩ ጉዳዮች ከተከሰቱ ሕጋዊ ምላሽ ለመስጠት ባንኩ ተገቢውን ዝግጅት ማድረጉንም ይጠቁማሉ።

ማሻሻያው ለኢትዮጵያን የተሻለ የፋይናንስ አቅም እንደፈጠረ አንስተው፤ ከአይኤምኤፍ እና ዓለም ባንክ የተገኘው ድጋፍና ብድርም ለሪፎርሙ ትግበራ እንደሚውል ነው ያስረዱት። አበዳሪ ተቋማቱ የሪፎርም ይዘት ጥራትና የኢትዮጵያን ምርታማነት አቅም በማየት ድጋፍና ብድር መስጠታቸውንም ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ ከሁለቱ አበዳሪ ተቋማት ባሻገር ከተለያዩ አጋር አካላት የርዕዮተ ዓለም ልዩነት ሳይገድባት ሪፎርሙን ለማስቀጠል የሚያስችል ሀብት ማግኘቷንም ነው ያስታወቁት።

አቶ ማሞ እንደሚያመላክቱት፤ መንግሥት የተለያዩ የፋይናንስ ሕግ ማሻሻያዎችንና አሠራሮችን በመተግበር የሪፎርሙን ውጤታማነት ለማስቀጠልም በትኩረት መሥራቱን ይቀጥላል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያውና የፓን አፍሪካ ንግድ ምክርቤት ዋና ኃላፊ ክቡር ገና በበኩላቸው፤ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት ማለት እኛ የማንቆጣጠረው ኃይል ገበያውን ይተምነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ አቅም ያለው አካል ብቻ ገበያውን እንዲመራው መፍቀድ ነው ይላሉ።

ማሻሻያው በተለይም የውጭ ምንዛሪን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብር በዓለም አቀፍ ግብይት ሥርዓት ውስጥ እንዲንሸራሸር የሚያደርግ ነው ያሉት አቶ ክቡር ገና፤ በዚህም የውጭ ምንዛሬውን እኛ እንድንቆጣጠረው የሚያደርግ አይደለም ሲሉ ይገልጻሉ ።

የቀድሞው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለውጭ ምንዛሬው ለእድገት የሚሆኑ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች የሚሰጡበት እንደነበር የሚያነሱት አቶ ክቡር ገና፤ እድገት ፈላጊ በሆነችና የኑሮ ውድነት ባለበት ሀገር ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት ውጤታማ ላይሆን የሚችልበት ዕድል ስላለ ቁጥጥሩን ማጠናከር እንደሚገባ ነው ሃሳባቸውን የሰጡት።

በመሆኑም የውጭ ምንዛሬ ቁጥጥር ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አመላክተው፤ በኢኮኖሚው ዘርፍ ያሉ አሠራሮችን በማሻሻል ጠንካራ አካሄድን መከተል እንደሚገባ ያስረዳሉ። በተለይም የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ሊያሳድጉ የሚችሉ አሠራሮችንና ምርታማነትን በማሳደግ እንደሀገር ውጤት ለማምጣት መሥራት እንደሚገባ ይገልጻሉ።



ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ

# የቢዝነስ ጉባዔው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያጠናክራል። ኢትዮጵያና ኦስትሪያ ጠንካራ የሚባልና ሁለንተናዊ ትብብር ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አላቸው። ጉባዔው የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ከማጠናከሩም በላይ በሀገራቱ መካከል ዓለም አቀፍ ትብብርን ያመጣል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፣ የቢዝነስ ጉባዔው ኢትዮጵያንና የኦስትሪያን በዲሎማሲው መስክ ያላቸውን ግንኙንት በንግድና ኢንቨስትመን ለመድገም ይረዳቸዋል። ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ጉባዔው የሥራ እድልን በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማሳደግ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ያጠናክራል። ኢትዮጵያን ከኦስትሪያን ጋር ያላትን ሁለንተናዊ ግንኙነት ለማጠናከር ቁርጠኛና ዝግጁ መሆኗንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት ያልተነካ ሀብት አላት ያሉት ሚኒስትሯ፣ ለአልሚዎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ጨምሮ የተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ለውጭ አልሚዎች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ በመሆናቸው የኦስትሪያ አልሚዎች መዋእለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ተግባራዊ እያደረገ የሚገኘው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አካታችና ዘላቂ እድገትን እያመጣ መሆኑንም ጠቅሰዋል። መንግሥት ኢትዮጵያ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የኦስትሪያ አምባሳደር ሲሞን ኬናፕ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ እና ኦስትሪያ ዘመናትን ያስቆጠረ ጠንካራ ግንኙነት አላቸው። የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት አንድ ምእተ ዓመትን ያስቆጠረ ነው፣ በያዝነው ዓመት የኦስትሪያ ኤምባሲ በአዲስ አበባ የተከፈተበትን 60ኛ ዓመት እንደሚያከብርም አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያና ኦስትሪያ በአርትና ባህል ጠንካራ ግንኙነት አላቸው ያሉት አምባሳደሯ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በከተማ መሠረተ ልማት፣ በኮንስትራክሽንና በሌሎች ዘርፎችም የቆየ ትስስር መኖሩን ገልጸዋል።

ይህንንም ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚሠራ አመልክተው፤ የኦስትሪያ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በንቃት እንደሚሳተፉ ተናግረዋል። በቀጣይ በንግድና ኢንቨስትመንት ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር በኦስትሪያ በኩል ሙሉ ቁርጠኛ መኖሩን ገልጸዋል።

የኦስትሪያ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ማልማት ይፈልጋሉ ያሉት አምባሳደሯ፣ በሜዲካል ላብራቶሪ፣ በፕላስቲክ ፣ በአግሮ ቢዝነስና በሌሎች ዘርፎች የመሠማራት ፍላጎት አላቸው። ኩባንያዎቹም በበርካታ ሀገራት የቆየ ልምድ ማካበታቸውን ጠቅሰዋል።

በጉባዔው ላይ የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይት እንደሚኖር የተገለጸ ሲሆን ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ሃላፊዎች ፣የኢትዮጵያና የኦስትሪያ የንግድ ማህበረሰብ ተገኝተዋል።

# ካፍ የኢትዮጵያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ ይህን በአፍሪካ እግር ኳስ ያላትን ታሪካዊ ድርሻ ከግምት በማስገባትም ከአምስት ዓመት በኋላ በ2029 የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት ጥያቄ ማቅረቧን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫውን ተጠቅማ የአፍሪካን እግር ኳስ ለማሳደግና በስፖርቱ ሀገር ለመገንባት እንደምትሠራ የተናገሩት ፕሬዚዳንት ታዬ፣ የአፍሪካ ዋንጫውን ለማስተናገድ ስታዲየሞችን እየገነባችና ያሉትንም ማሻሻያ እያደረገችባቸው እንደምትገኝ ገልጸዋል።

የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሞትሴፔ (ዶ/ር) በሰጡት መግለጫ፤ ኢትዮጵያ ያቀረበችው የአፍሪካ ዋንጫ አስተናጋጅነት ጥያቄ ካፍ ባለው የአሠራር ሥርዓት እንደሚታይ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ እግር ኳስ ውስጥ ታሪካዊ ሚና እንዳላትና የካፍ መሥራች አባል መሆኗን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ነጻነት ትልቅ ሚና የተጫወተች ሀገር እንደሆነች አንስተዋል።

"የኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ የማስተናገድ ጥያቄዋን ያቀረበችው በትክክለኛው ጊዜ ነው" ያሉት ሞትሴፔ፤ ኢትዮጵያውያን ለእግር ኳስ ያላቸው ስሜትና ቁርኝት ከፍተኛ መሆኑን እንደሚረዱና ይህም ሕዝቡን አንድ የሚያደርግ ትልቅ አቅም መሆኑን አብራርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ እየተገነቡ ያሉ ስታዲየሞችና የስፖርት መሠረተ ልማቶችን እንዳስጎበኟቸውና ባዩት ነገር መደሰታቸውንም አክለዋል። ኢትዮጵያ የካፍን መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በስኬት ማስተናገዷን ገልጸው፣ የኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይነትም አድንቀዋል።

ኢትዮጵያ ከቀናት በፊት የ2029 አፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ለካፍ በይፋ ጥያቄ ማቅረቧ የሚታወስ ሲሆን፣ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለካፍ ጠቅላላ ጉባዔ ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ ልዑካን በታላቁ ቤተ-መንግሥት የእራት ግብዣ ባደረጉበት ሥነሥርዓት ላይ ኢትዮጵያ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማስተናገድ አቅም እንዳላት ተናግረዋል። የካፍ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትንም እየተገነባ የሚገኘውን የብሔራዊ ስቴድየም ካስጎበኙ በኋላ በፅህፈት ቤታቸው አነጋግረዋል።

የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙትሴፔ (ዶ/ር) በእራት ግብዣው ላይ በኢትዮጵያ ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበል ምስጋና አቅርበው፤ የኢትዮጵያውያን ባህል፣ እሴትና እንግዳ ተቀባይነት "ኢትዮጵያ ቤታችን እንደሆነች እንዲሰማን አድርጎናል" በማለት ተናግረዋል። የፊፋ ፕሬዚዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖም "የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ የኛም ሀገር ነች" ሲሉ ተናግረዋል።

ካፍ የኢትዮጵያን ጥያቄ በተመለከተ በቀጣይ ዓመት ሞሮኮ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ እንደሚሰጥ ይጠበቃል።

# “ሰውን መጉዳት

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔን ሲያስጀምሩ እንደገለጹት፤ በሀገራችን አለመግባባት፣ ማኩረፍና መቀያየም በዝቷል። ችግሩም ከሕዝብ አልፎ የአምልኮ መፈጸሚያ ቦታዎችንና የአምልኮ ፈጻሚዎችን ኢላማ ያደረገ ነው።

ይህ አይነቱ ተግባር ለሀገርና ሕዝብ የውድቀት ምክንያት ከመሆን ባለፈ የዕድገት ምልክት ሊሆን እንደማይችል ገልጸው፤ ይህ ክፉ ድርጊት እየተፈጸመ ያለው በእኛው ልጆች መሆኑ ደግሞ የበለጠ ያሳዝናል ብለዋል።

በከተማም፣ በጫካም፣ በገጠርም በየትኛውም ስፍራ የምትገኙ ልጆቻችን ምንም ይሁን ምን ሀገርንና ሕዝብን ከመጉዳት ተቆጠቡ ሲሉ አሳስበዋል።

በተለይም ከቤተክርስቲያንና ከሀገር እንደዚሁም ሕዝቡን ከሚያገለግሉ ካህናትና ሲቪል ሠራተኞች እባካችሁ እጃችሁን አንሡ ሲሉ ጠይቀዋል።

ሰውን መጉዳትና እግዚአብሔርን መዳፈር በማቆም ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እድል ስጡ ሲሉ አባታዊ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ክፉው መንፈስ በተራቀቀና በተራዘመ ስልት ሊውጠን በተነሣ ልክ እኛም ከእሱ እጥፍ በሆነ መለኮታዊ ኃይል ልንመክተው ካልቻልን በፈጣሪም ሆነ በትውልድ እንደዚሁም በታሪክ ፊት በኃላፊነት መጠየቃችን አይቀርም ሲሉ አስታውቀዋል።

ችግሩን መከላከል የምንችለው ሕዝቡን በደምብ በማስተማርና በመጠበቅ፣ ለመሪነታችን ዕንቅፋት ከሚሆኑን ዓለማዊ ነገሮች ራሳችንን በማራቅ እንዲሁም ሕዝቡን መስለን ሳይሆን ሆነን ስንገኝለት ነው ብለዋል።

የምናስተምረው ሌላ የምንሠራው ሌላ ከሆነ ከሕዝቡ አእምሮ መውጣታችን እንደማይቀር መገንዘብ አለብን ያሉት ፓትሪያሪኩ፤ በመሆኑም በሰብእናችን፣ በአስተዳደራችን፣ በአመራራችንና በጥበቃችን ሁሉ እንደቃሉ ለመፈጸም መትጋትና በቁርጥ መነሣት ጊዜው አሁን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ይህ ሲሆን በምእመናንና በእኛ መካከል ያለው ግንኙነት አስተማማኝና እንከን የለሽ ከመሆኑም ባለፈ የመሪነት፣ የእረኝነትና የመልካም ተምሳሌነት ኃላፊነታችንን በትክክል ተወጥተናል ማለት እንችላለን ነው ያሉት።

ዓለማዊው አስተዳደር የተመቻቸ መደላድል ሊፈጥርላቸው ግድ ነው ያሉት ፓትሪያሪኩ፤ ዓለማዊው አስተዳደርም የመለኮትን ተልእኮ ለመፈጸም የተሾመ ሹመኛ እንደመሆኑ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክል መምራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚካሄዱት የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባዔት አንዱ የጥቅምት 2017 ዓ.ም ጉባኤ ሲሆን፤ ምልዓተ ጉባዔው በቤተክርስቲያኒቷና በሀገራዊ ዓበይት ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አጀንዳዎችን አውጥቶ በዝግ ላልተወሰኑ ጊዜያት ሲወያይ እንደሚቆይ አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተመድ የአፍሪካውያን ድምጽ የመሆን ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል!

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ)፣ ስያሜው የዓለም ሕዝቦች ድምጻቸው የሚሰማበት፤ ጥቅምና ፍላጎታቸው የሚከበርበት፤ ተሳትፎና ውክልናቸው ያለ አድሎ በፍትሃዊነት የሚገለጥበት መድረክ መሆኑን ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስምና ግብሩ እየተነጣጠሉ፤ የዓለም መንግሥታት መድረክ መሆኑ ቀርቶ የጥቂት ኃያላን ፈላጭ ቆራጭነት ጎልቶ የሚታይበት ሆኗል፡፡

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ የኃያላኑ ጉዳይ አስፈጻሚ የሆኑ አንጃዎች በፈለጉት ሰዓት የፈለጉትን ነገር ሲፈጽሙም፤ ሲፈጸምላቸውም የሚታየው፡፡ በአንጻሩ ለእነዚህ ኃያላን ጥቅምና ፍላጎት ሳይሆን ለሀገራቸውና ሕዝቦቻቸው ታምነው የሚንቀሳቀሱ ሀገራት መንግሥታትን በእጅጉ ሲወገዙ፤ አለፍ ሲልም በማዕቀብ ሲናጡ፤ ከፍ ሲልም ይፋዊ የቀጥታና የእጅ አዙር የጦርነት አዙሪት ውስጥ እንዲናውዙ ሲደረግ የሚስተዋለው፡፡

አፍሪካም፣ በዚህ ረገድ ከሚጠቀሱ እና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መድረክ ላይ ከስም የዘለለ ይሄ ነው የሚባል ተሳትፎም፤ ተደማጭነትንም ተነፍጋ የምትገኝ አህጉር ናት፡፡ አፍሪካውያን (ሕዝቦችም፣ መንግሥታትም) ከመድረኩ ሊኖራቸው የሚገባ ተሳትፎና ውክልና የማይገባቸው ተደርገው የተቆጠሩበት፤ ከዚህ የተነሳም ከፍ ላለ ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎችም የሰላምና ፀጥታ ችግሮች ጫና ውስጥ እንዲገቡ ተደርገው ቆይተዋል፡፡

ምክንያቱም፣ ምንም እንኳን አፍሪካ የሃምሳ አራት የአፍሪካ መንግሥታት አህጉር፤ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ተመድን የመሠረቱ ሀገራት ምድር፤ ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን በላይ (ያውም አምራች እና ትኩስ ኃይል የሆነው ወጣት የበዛባት) ሕዝብ፤ ከፍ ያለ የተፈጥሮ ሀብት እና የመልማት እምቅ አቅም ያላት ብትሆንም፤ ይሄን ሁሉ ከፍ ያለ አቅም ባለቤትነቷን የሚመጥን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ተሳትፎም፣ ተደማጭነት የሚያስገኝላትን ሥፍራም ማግኘት የማይጨበጥ ሕልም ሆኖባት ዘልቋል፡፡

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ አፍሪካውያን ሃምሳ አራት ሆነው እንደ አንድ በመቆጠር የአንድ ለብዙ መድረኮችን በመጠቀም ድምጻቸውን ለማሰማትና የልማት አቅማቸውን አውጥቶ ለመጠቀም ሲጥሩ የሚታየው፡፡ ለዚህም ነው አፍሪካውያን ኃያል ነን በሚሉ፣ ነገር ግን ኢፍትሃዊነትን ባነገቡ ሀገራትና ተቋሞቻቸው አማካኝነት የሚመጣን ፖለቲካዊም፣ ኢኮኖሚያዊም ሸክም በጫናቃቸው ላይ ለማኖር የተገደዱት፡፡

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ አፍሪካውያን በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት መታየት የሌለባቸው የልማት ጉዳዮቻቸው ጭምር አጀንዳ ሆነው እየቀረቡ የመልማት ጉዟቸው እንዲደናቀፍ ሲሠራ የሚታየው፡፡ ለዚህም ነው አፍሪካውያን በፈጸሙት ተጋድሎ የተጎናጸፉትን የነጻነት ብርሃን፤ በሌላ ቅኝ ገዥነት እሳቤ አፍሪካን ድጋሚ ለመቀራመት የሚደረገው እሽቅድምድም ጎልቶ የሚስተዋለው፡፡

እነዚህ አይነት ፖለቲካን፣ ኢኮኖሚን፣ ዲፕሎማሲን፣ ሰላምና ፀጥታን፣... ማዕከል አድርገው የሚደረጉ የእጅ አዙር አፍሪካን የማተራመስ፤ የማዳከም እና አቅም ነስቶ ዳግም በሌላ የቅኝ ግዛት ማዕበል ለመናጥ የሚደረግ እሽቅድምድም ግን፤ ዛሬ ላይ አፍሪካውያን የሚቀበሉትም፤ የሚሸከሙትም አይደለም፡፡

አፍሪካውያን ከትናንቱ ተምረዋል፤ በመሪዎቻቸውም፣ በአርቆ አሳቢ ልጆቻቸውም ታግዘው ስለ ነጋቸው ተልመው ዛሬን ጉዞ ጀምረዋል፡፡ ከዚህም በላይ ለልማታቸው፣ ለሰላምና ፀጥታቸው፣ ለዲፕሎማሲ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮቻቸው የሌሎችን ውሳኔና ይሁንታ ከመጠበቅ መውጣት እንዳለባቸው ስለሚያምኑም፤ አፍሪካውያን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ባሉ አደረጃጀቶች ሁሉ ተገቢውን ውክልና ለማግኘት የሚያስችላቸውን ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

ይሄ ጥያቄ ደግሞ ለመጠየቅ ያህል የቀረበ አይደለም፡፡ ይልቁንም አፍሪካውያን የሳራቸውን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ የዓለም ሁሉ ጉዳይ ግድ ይላቸዋል እና በዚህ ላይ መምከርም መወሰንም የሚያስችላቸውን የቬቶ ፓወር ውክልናም ጭምር ማግኘት እንዳለባቸው አበክረው ያምናሉ፡፡ ይሄንኑም እንዲፈጸም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን አሳስበዋል፡፡

ይሄ ጥያቄያቸው ታዲያ ሊደመጥ ብቻ ሳይሆን ተመዝኖ በልኩ መልስ ሊያገኝ የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም አፍሪካ በሁሉም መስክ ይሄን ጥያቄዋን መልስ እንድታገኝ የሚያስገድድ አያሌ ጉዳዮች አሏትና ነው፡፡ ከሰሞኑም የአዲስ አበባ ለይፋዊ ጉብኝት የተገኙት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬስም ይሄንኑ እውነት የተገነዘቡ ይመስላል፡፡

ዋና ፀሐፊው ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ከኢፌዴሪ ፕሬዚዳንትም ሆነ ከአፍሪካ ሕብረት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በነበራቸው ውይይት በዚሁ ጉዳይ ላይ መምከራቸውን ጠቁመዋል፡፡ መጠቆም ብቻም ሳይሆን፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለአፍሪካውያን ተሳትፎም ሆነ ተጠቃሚነት እውን መሆን፤ ለሕብረቱም ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ማግኘት፤ አፍሪካ ላይ ለሚፈጸም ማናቸውም ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ በተለይም ጊዜውን በማይመጥን የፋይናንስ ተቋማት አማካኝነት በአፍሪካ ኢኮኖሚ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ደባ ከመከላከል አኳያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከአፍሪካ ሕብረት ጋር በቅርበትም፣ በጋራም እንደሚሠራ አረጋግጠዋል፡፡

ይሄ የዋና ፀሐፊው ገለጻ ተገቢም፤ ለተመድ እንዲወጣ የሚጠበቅ ቃል ነው፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እነዚህን ጉዳዮች ማዕከል ባደረገ መልኩ ከአፍሪካ ሕብረት ጋር በቅርበት መሥራት፤ የአፍሪካውያን ጥያቄ በልኩ ተገንዝቦም ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ አበክሮ መሥራት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ መሆኑን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ መትጋት ይገባዋል፡፡


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## "የሚያበላህ ይቆጣጠርሃል!"

ዮናታን ጠለሰው ብዙነህ

ለጽሁፌ መነሻ ሃሳብ ይሆነኝ ዘንድ "የሚያበላህ ይቆጣጠርሃል! "He who feeds you, controls you!" የሚለውን የቀድሞውን የቡርኪናፋሶ ፕሬዚዳንት ካፒቴን ቶማስ ሳንካራ የምንጊዜም ምርጥ አባባል ወስጃለሁ፡፡ ይህ የቶማስ ሳንካራ ንግግር አፍሪካ ውስጥ ያለውን እውነታ እስካሁን በተጨባጭ የሚያመላክት ነው፡፡

አብዮተኛው ቶማስ ሳንካራ የአፍሪካን ኢንዲፔንደንስ ፓርቲን ወክሎ እ.ኤ.አ ከ1983 እስከ 1987 የምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ቡርኪናፋሶ አምስተኛው ፕሬዚዳንት ሆኖ አገልግሏል፡፡ ለሀገሩ ያለውን ታማኝነት እና ፍቅር እስከ ሞት በዘለቀ መስዋእትነቱም አስመስክሯል፡፡ የሀገሪቱን ጦር በመቀላቀል እ.ኤ.አ ከ 1966 ዓ.ም አንስቶ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ አገልግሏል፡፡

እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ታይቶ የጠፋው ቶማስ ሳንካራ የቡርኪናፋሶ ታላቅነት እንዲረጋገጥ በነበረው ጥልቅ ምኞት ወደ ሥልጣን በመጣ ማግስት ጀምሮ በሀገሪቱ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ሪፎርሞችን ጨምሮ በርካታ የለውጥ አስተሳሰቦችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ገና በ33 ዓመቱ ወደ ሥልጣን የወጣው ሳንካራ፣ በዓመቱ የሀገሩን መጠሪያ ስም ከአፐር ቮልታ ሪፐብሊክ ወደ ቡርኪናፋሶ ቀየረ፡፡ ይህም ለጀመረው ሁሉን አቀፍ ለውጥ እንደ አንድ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ሀገሩ ቡርኪናፋሶ ራሷን የቻለች መሆን እንዳለባት ያመነው ቶማስ ሳንካራ፣ "የሚያበላህ ይቆጣጠርሃል!" በሚለው የለውጥ ሃሳቡ ርዳታን እና ከመጠን ያለፈ ብድርን ተከትሎ የሚመጣው እጅ ጥምዘዛ የሀገር እና የሕዝብን ፖለቲካዊ ነጻነት እንደሚፈታተን ለማስረዳት ሞክሯል፡፡

ራስን መቻል፤ በተለይም በምግብ ራስን የመቻል ጉዳይ የፖለቲካ ነጻነትን ምሉእ ለማድረግ ትልቅ አቅም መሆኑን በመግለጽ፤ ሀገሩ በምግብ እህል እራሷን መቻል እንደሚኖርባት በስፋት ለማስገንዘብ ሞክሯል። አስተሳሰቡን መሠረት ያደረጉ የለውጥ ሥራዎችንም ሠርቷል ።

ይህ አፍሪካዊ የለውጥ ሃዋርያ፤ ያሰበውን ማሳካት ባይችልም፤ እንደ አንድ የለውጥ መሪ በወቅቱ ያነሳው ይህ ሃሳብ ዛሬ ድረስ ትልቅ የፖለቲካ እውነታ ተደርጎ ይወሰዳል። ጉዳዩ በምግብ እህል እራሳቸውን ላልቻሉ ሀገራት እስካሁን ፈተናም ሆኖ ቀጥሏል። ለበለጸጉ ሀገራትም ያሻቸውን የማዘዣ እና የማስፈፀሚያ ካርድ ሆኖ እስከ ዛሬ ዘልቋል፡፡

ለመሆኑ ራስን በምግብ መቻል /Food and Nutrition Security/ ማለት ምን ማለት ይሆን?

በምግብ ራስን መቻል የሚባለው ፅንሰ ሃሳብ የተፈጠረው እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ አጋማሽ እንደሆነ የዓለም አቀፉ የምግብ እና የግብርና ድርጅት ፋኦ (FAO) መረጃ ያስረዳል፡፡ እ.ኤ.አ በ1974 ዓ.ም የዓለም የምግብ ድርጅት ስብሰባ 'ዎርልድ ፉድ ሰሚት' የመጀመሪያ ትኩረት በመጠን እና በአቅርቦት ላይ ነበር። በምግብ ራስን መቻልን ሲተረጉመውም፣

"Availability at all times of adequate world food supplies of basic foodstuffs to sustain a steady expansion of food consumption and to offset fluctuations in production and prices."

በግርድፉ ወደ አማርኛ ስንመልሰው "በሁሉም ጊዜ የምናገኘው በቂ ዓለም አቀፍ የምግብ አቅርቦት ለዘላቂ የምግብ ፍጆታ ስርጭት እንዲሁም ለምርት እና ዋጋ መዋዠቅ መፍትሄ፡፡" ሲል ፈቶታል ይለናል፡፡

ይህ ትርጓሜ እ.ኤ.አ በ1983 ዓ.ም ማሻሻያ የተደረገበት ሲሆን በተለይም እ.ኤ.አ በ1986 ዓ.ም በከፍተኛ ደረጃ ተፅእኖ ፈጣሪ የነበረውን "Poverety and Hunger" /ድህነት እና ረሃብ/ የተሰኘውን የአለም ባንክ ሪፖርት ተከትሎ "Access of all people at all times to enough food for an active, healthy life". "ጤናማ ለሆነ ሕይወት ለሁሉም ሰው የሚያስፈልግ የምግብ አቅርቦት" በሚል አዳብሮታል፡፡

በአባወራ ደረጃ የሚወርደው በምግብ ራስን የመቻል እሳቤ፤ ሰዎች በቂ ምግብ ለማግኘት አካላዊ፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት እስካለባቸው ድረስ በምግብ ራስን መቻል የሚባለው ጉዳይ ተጨባጭ አይሆንም ሲል ያትታል፡፡ አተገባበሩ ላይ ከተጠቀሱት ተግዳሮቶች መካከል ደግሞ ኢኮኖሚያዊውን የምግብ መልክ ገልጠን የታዳጊ ሀገራትን ተጨባጭ መረጃዎች እንቃኝ፡፡

**ይህንን ጥረት አስቀጥለን በቅርቡ ሀገራችንን ከምግብ ርዳታ ጥገኝነት የምናላቅቅበት መንገድ ላይ እንዳለን መስካሪ የሚያሻው ጉዳይ አይደለም**

### የምግብ ወጪያች ከአጠቃላይ ወጪያችን ምን ያህሉን ይሸፍናል?

እንደ ባዮሜድ ሴንትራል የቅርብ ወራት መረጃ በታዳጊ ሀገራት በተለይም ከሳህራ በታች ባሉ ሀገራት የምግብ ወጪ ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ ይኸውም ከ65% በመቶ እስከ 70% በመቶ የሀገራቱን የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) እንዲሁም 70% በመቶ የሚሆነውን የአንድ ቤተሰብ ወጪ ይሸፍናል፡፡

ሌላኛው የሳህል ቀጣናን እና የአፍሪካ ቀንድን የሚዳስስ የዓለም ባንክ ዘገባ ደግሞ በቡርኪናፋሶ፣ በቻድ እና በማሊ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ሰዎች በራሽን እንደሚደገፉ ሲገልፅ፤ እ.ኤ.አ ከ2017 አስከፊ ረሃብ በኋላ በተደረገላት ድጋፍ ሶማሊያ ቤተሰቦች በቀን ለሁለት ጊዜ መመገብ በማስቻል ለውጥ ማስመዝገቧን ይገልፃል፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ውስጥ የሚገኙ ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን ሰዎች በአስከፊ ሁኔታ የምግብ ዋስትና የሌላቸው መሆኑን የሚያስነብበው ዘገባው፣ ኬንያ እና ሶማሊያን የመሳሰሉ የቀጣናው ሀገራት ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ አይተውት የማያውቁት አይነት ድርቅ እንዳጋጠማቸው ይጠቁማል፡፡

በዚህ ተጨባጭ እውነታ ስር የምትካተተው ኢትዮጵያም ስምንት ሚሊዮን ያህል ዜጎቿ በምግብ እና በገንዘብ ድጋፍ ስር እንደሚገኙ የዓለም ባንክ ዘገባ ገልፆ፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በስፋት እያከናወነችው ያለውን በራስ ጥረት ምግብ የማምረት እና የአረንጓዴ ዐሻራን አይነት ስኬታማ ጉዞ ለሁሉም ቀጣናዎች መፍትሄ ነው ሲል ያስቀምጠዋል፡፡

ይህንኑ ነጥብ የሚደግፈው የዓለምአቀፉ የምግብ ፕሮግራም (WFP) ዘገባ፣ ለኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አሁንም ዋና ትኩረቷ እንደሆነ በማስታወስ፣ በአሁኑ ጊዜም ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ያልተስተዋለ አመርቂ ሥራ በድህነት ቅነሳ እና በመሠረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ ሰርታለች ሲል አስነብቧል፡፡

ይህንን ጥረት አስቀጥለን በቅርቡ ሀገራችንን ከምግብ ርዳታ ጥገኝነት የምናላቅቅበት መንገድ ላይ እንዳለን መስካሪ የሚያሻው ጉዳይ አይደለም፡፡ ለተከታታይ ዓመታት የተሰራባቸውን የኩታ ገጠም የእርሻ ዘዴ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሳንዘነጋ፣ ከሰሞኑ በሐረሪ ክልል ያስተዋልነው ፈጥኖ ደራሽ የማሽላ ምርት እንዲሁም ተስፋ ሰጪው የአማራ ክልል የሩዝ ምርታማነት የያዝነውን መንገድ ውጤታማነት ያመላክታል፡፡

በቤተሰብም ደረጃ ቢሆን እንዴት አድገን ራሳችንን ከምግብ ጥገኝነት እናላቅ? ብለን ብንጠይቅ ብዙዎች የሚሰጡን ምላሽ ምግብን በተቻለ መጠን፣ በተገኘ አስቻይ ክፍት ቦታ ሁሉ ማምረት እንደሚገባን ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከጤናችን አንስቶ እስከ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች መቋቋሚያነት ድረስ የተዘረጋው መፍትሄ፣ ቢያንስ ለራሳችን የሚሆን የጓሮ አትክልት ማምረት መጀመራችን እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህም በጓሯችን፣ በእጃችን የሚገኝ ወርቅ መሆኑን ተገንዝበን ለተሻለ የነገ መዳረሻ ታላቅ የግብርና አብዮት ከየቤታችን መጀመር እንደሚገባን የሚያመላክት ነው፡፡

እንደ ሀገር ይህን ማድረግ ካልቻልን ግን ታላቁ ቶማስ ሳንካራ እንዳለው "የሚያበላህ ይቆጣጠርሃል" ነውና፣ እጣ ፈንታችን፣ በሌሎች በርዳታ ስም ያሻቸውን እንዳሻቸው ከሚዘውሩ 'የጠገቡ' ሀገራት እጅ ላይ እንደሚወድቅ ለመገመት የሚከብድ አይደለም፡፡

# ‹‹ ከየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ በ15 ደቂቃ ልዩነት ውስጥ መረጃዎችን ወደ ማዕከል ማስገባ የሚያስችል ስርዓት ተፈጥሯል ››

- አቶ ፈጠነ ተሾመ፣
የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ሞገስ ተስፋ እና መክሊት ወንድወሰን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት እንደ ተቋም በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ፤ የተለያዩ አደረጃጀቶችና ሥያሜዎችም የነበሩት ነው፤ በ1973 ዓ.ም ራሱን ችሎ በአዋጅ ከመቋቋሙ በፊት፣ በሲቪል አቬዬሽን ስር ነበር:: በአሁኑ ሰዓትም የኢትዮጵያን የአየር ጸባይ ሁኔታና አዝማሚያዎችን በመተንበይ፤ በመረጃ የተደገፈ የአየር ሁኔታን ለሕዝብና ለባለድርሻ አካላት እያደረሰ ይገኛል::

በዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን በዚሁ ተቋም ላይ በማተኮር፤ የቅድመ ማስጠንቀቂያ የአየር ጠባይ ትንበያን መረጃን የማቅረብ ደረጃውን፤ ወቅቱ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ በመታጠቅ የአየር ጠባይ ትንበያን ተደራሽ የማድረግ ተግባሩን፤ የተደራጀና ተከታታይ መረጃዎችን በመሰነድና በመተንተን ውጤታማ የትንበያ አሰራር ሥርዓት እውን ከማድረግና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በማተኮር፤ ከኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ጋር ያደረግነውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል::

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ ዋና ትኩረቱ አድርጎ የሚሰራው ምንድን ነው?**

**አቶ ተሾመ፡-** ኢንስቲትዩቱ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ የኢትዮጵያ መልካምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ የሜትሮሎጂ መረጃ መሰበሰቢያ ጣቢያዎችን ማቋቋም ነው:: ሁለተኛው፣ ከተቋቋሙት ጣቢያዎች መረጃዎችን መሰብሰብ ነው:: ሥስተኛው፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች የጥራት ቁጥጥር እና ክትትል በማድረግ በብሔራዊ መረጃ ቋት ውስጥ በመደረጃት፣ ለምርምር ተቋማት፤ ለውሳኔ ሰጭ አካላት፤ መረጃዎችን ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ነው::

እራሱም እንደ ተቋም እነዚህን መረጃዎች መሰረት በማድረግም የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የአየር ትንበያና የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን ይሰጣል:: የተሰጡ ትንበያዎችን መሰረት በማድረግም ለግብርና፤ ለውሃ፤ ለጤና፣ ለአቬሽንና መሰል ዘርፎች ምክረ ሀሳቦችን ይሰጣል::

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ አሁን ላይ ያለው የትንበያ እና የመረጃ ተደራሽነት አቅሙ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደራሽነቱን እያሳደገ፤ የመረጃ አቅርቦቱንም እያሰፋ መጥቷል:: ቀደም ሲል የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎቻችን የገጸ ምድር (መሬት ላይ ያሉ) ጣቢያዎች ብቻ ነበሩ:: ይህም የኢትዮጵያን መልካዓምድራዊ አቀማመጥን መሰረት በማድረግ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ብቻ ያተኮሩ ነበሩ:: አሁን ላይ ይህን ሁኔታ በመቀየር በሁሉም አካባቢዎች የሜትሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን የማስፋት ስራ ሰርቷል::

ከጊዜ ወደ ጊዜ የሜትሮሎጂ መረጃ ጣቢያዎች ቁጥራቸው እያደገ በመምጣቱ በአሁኑ ጊዜ በገጸ ምድር በሰው መረጃ የሚሰበሰብባቸው ጣቢያዎች አንድ ሺህ 372 ደርሰዋል:: አውቶማቲክ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ደግሞ 300 ደርሰዋል:: ይህም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ አቅም እየተገነባ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ያላትን የመልካዓምድር አቀማመጥ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በዝቅተኛ፤ በደጋማ፤ በወይና ደጋማ አከባቢዎች ጣቢያውን የመገንባት ስራ ተከናውኗል:: በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠው የምክረ ሀሳብ፤ የትንበያና የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የክልል ሜትሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተቋቁመዋል::

በኦሮሚያና በአማራ ክልል ሶስት ሶስት ቅርንጫፍ ማዕከላት፤ በኦሮሚያ ጅማ፣ አዳማ እና ባሌ-ሮቤ፤ በአማራ በኮምቦልቻ፣ ባሕርዳር፣ ምዕራብ አማራና ምስራቅ አማራ፤ በሌሎች ክልሎች ደግሞ በእያንዳንዳቸው አንዳንድ ጣቢያዎች ተቋቁመው እየሰሩ ነው:: እነዚህ ጣቢያዎች ጂኦግራፊያዊም ይሁን የፖለቲካዊ ድንበር ሳይገድባቸው መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ይሰጣሉ:: ስለዚህ በእኛ ግምገማ ተደራሽነቱ ጥሩ ደረጃ ላይ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ከቁጥር ባለፈ ጥሩ ደረጃ ላይ መድረሱን እና ውጤት ስለመኖሩ መለኪያዎቹ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ሁለቱም ጽንፍ የረገጡ የአየር ጠባይ (climate extremes) ብለን የምንጠራቸው የአየር ጸባዮች ኢትዮጵያ ውስጥ ያጋጥማሉ:: የዓለም አቀፍ ኢሊኖ ወይም ላሊና ተጽዕኖ በሀገራች ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋል:: በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በሕንድና በሜድትራንያን፤ በፓሲፊክ እና በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ የሚስተዋሉ የባህር መሞቅና መቀዝቀዝ በኢትዮጵያ የሚኖረው የአየር ሁኔታን ከመወሰን አንጻር አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ::

ኢንስቲትዩቱ እነዚህ የአየር ጸባይ ዓለማቀፋዊ የሜትሮሎጂ ክስተቶችን በመተንተን፤ በሀገር ውስጥ በተተከሉት የአየር ትንበያ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች የሚገኙ የረጅም ጊዜ መረጃዎችን ወደ ኋላ ሂዶ በመተንተን፣ ኢትዮጵያ የምታስተናግዳቸው ወቅቶች መሰረት በማድረግ እንደ ሀገር ሊከሰት የሚችለውን የአየር ሁኔታና ጸባይ ቀድሞ መረጃው ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል::

ለምሳሌ ኢትዮጵያ በጋ፤ ክረምት፤ በልግ ተብለው እያንዳንዳቸው አራት አራት ወራትን የያዙ ወቅቶችን ታስተናግዳች:: ስለዚህ የበጋ ወቅት ከመግባቱ በፊት ለባለድርሻ አካላት ባሉበት መረጃው ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል:: በጋ ብለን ስጠራ ከጥቅምት ጀምሮ እስከ ጥር ያሉትን አራት ወራት የሚያጠቃልል ነው:: በልግ ደግሞ ከየካቲት ጀምሮ እስከ ግንቦት ያሉትን ወራት ያካትታል:: ክረምት ተብሎ የሚጠራው ከሰኔ ጀምሮ እስከ መስከረም ያሉትን አራት ወራቶች የሚያጠቃልል ነው::

እነዚህ ወራቶች ከመግባታቸው በፊት ከሕብረተሰቡ ጀምሮ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በአካል ጭምር በመገናኘት መረጃው እንዲያገኝ ይደረጋል:: የተሰበሰበው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖን በማሳየት የትንበያ መረጃ ይሰጣል:: በግብርና፤ በውሃ፤ በጤና ዘርፎች ላይ ሊያመጣ የሚችለውን በጎም ሆነ አሉታዊ ጫና የሚቀርብበት ሁኔታ አለ::

በተጨማሪ የውሳኔ ሰጭ አካላት በብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ውስጥ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ምክር ቤት አለ:: በምክር ቤቱ ውስጥ የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አባል ሆኖ መረጃዎችን ለውሳኔ ሰጭ አካላት፤ ለክልል ፕሬዚዳንቶች፤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የፌደራል ሚኒስቴር ተቋማት ባሉበት ምን አይነት የአየር ሁኔታ ጸባይ እንዳለና አሉታዊና አዎንታዊ ጫና እንዳለው ገለጻዎች ይሰጣሉ:: ይህን መረጃ ፖሊሲ አውጪው ወስዶ ከራሱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ በግብርና፤ በውሃ፤ እና በጤና፤ ላይ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት የሚለውን አቅጣጫ ይሰጣል::

የመረጃ ተደራሽነቱ በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እናረጋግጣለን፤ በመገናኛ ብዙሃን በኩልም መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ እንሰራለን:: በታችኛው አስተዳደር እርከን የሚገኙ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ከግብርና ሚኒስቴር፤ ከውሃ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት መረጃ ሕብረተሰቡ እንዲያገኝ ይደረጋል:: በዚህ መልክ ተደራሽነቱን እለካለን:: በዚህም የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ ተችሏል:: ለባለድርሻ አካላት ቃለመጠይቅ በማድረግና ሰርቬይ በመተንተን ጭምር ውጤታማነቱን እናረጋግጣለን::

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ እንደ ድርቅ፣ ጎርፍና የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋዎች ተከስተው ጉዳት ተስተናግዷል:: ተቋማዊ የትንበያ አቅማችሁ ውጤታማ ከሆነ እነዚህን ለምን ቀድሞ መገንዘብ አልተቻለም? ሙከራው ከነበረስ አደጋን በመቀነስ ረገድ የነበራችሁ አስተዋጾስ ምን ነበር?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ከአየር ጠባይና ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አደጋዎች የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ እየፈተነ ነው:: አደጋው ማስቀረት በተአምር አይቻልም:: ለምሳሌ፣ በቅርቡ በአሜሪካ ፍሎሪዳ የተከሰተው አውሎ ንፋስ ሀሪኬን መሰረት ያደረገ ከፍተኛ የሆነ ውድመት አድርሷል:: ስለዚህ እንደዚህ አይነት አደጋዎች መከሰታቸው አይቀርም:: ሆኖም የአየር ጠባይ ለውጥን ተጽዕኖን መቀነስ የሚቻልባቸው መንገዶች አሉ::

ለዚህ ግን የሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንዲሁም የሀገሪቷን የመልከዓምድርና የወቅቶች ስብጥር ማየት ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም፣ አንዳንድ ጊዜ ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ ይከሰታል:: በሌላ ጊዜ ድርቅ ወይም የዝናብ እጥረት የሚያጋጥምበት ሁኔታዎች አሉ:: ይህ ይለያያል::

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዝሃ የሆነ የአግሮ ኢኮሎጂካል ዞን አለ:: ለምሳሌ ከመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ጀምሮ ከፍ ያሉት አከባቢዎች ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ክረምት ነው:: የምዕራብ የሀገሪቱ ከተሞች ደግሞ «ሞኖሞዳል» የአንድ ወቅት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ናቸው:: ሰሜን-ምስራቅ የሀገሪቱን ክፍል ብንወስድ ደግሞ አፋር፤ ምስራቅ አማራ፤ ምስራቅ ኦሮሚያ፤ ምስራቅ ትግራይ ብወስድ ደግሞ በልግ ሁለተኛ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው::


ፎቶ- ዳኜ አበራ

የደቡብ የሀገሪቱን ክፍል አጋማሽ ስንወስድ ደግሞ በክረምት ወቅት ምንም ዝናብ የማያገኝ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆነ ሲሆን በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው:: ስለዚህ ብዝሃ የሆነ የአየር ጠባይ እና ሁኔታ የሚስተዋልበት አካባቢ ነው:: ከነዚህ አካባቢዎች ጋር የተጣጣመ አገልግሎት እየሰጠን ነው:: ከኢንስቲትዩቱ የሚጠበቀውም ከእነዚህ የሚገኘውን መረጃ መስጠት እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ነው:: እያንዳንዱ ተቋም ካላቸው ነባራዊ በሁኔታ አንጻር ዝግጅት ያደርጋሉ::

ለምሳሌ፣ የጤናው ዘርፍ የአየር ሁኔታው ለዋባ ስርጭት ምቹ ነው? አይደለም? የሚለውን ተንትኖ ወረርሽኙን መግታት የሚችልበት መረጃ እንዲያገኝ እናደርጋለን:: ግብርናም በተመሳሳይ ዝናብ ቶሎ ገብቶ ዘግይቶ የሚወጣ ከሆነ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ሰብሎችን መዝራት ብቻ ሳይሆን፤ ምን አይነት ሰብልም መዝራት እንዳለበት ይወስናል::

ቦረና ላይ ባለፈው ድርቅ እንደነበር ይታወቃል:: ለተከታታይ ዓመት ዝናብ አልነበረም:: የድርቁን ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል የትንበያ መረጃዎቹን ለማድረስ ስራዎች ተሰርቷል:: ባለፈው የነበረው ድርቅ በዚህ ዓመት ለሌሎች አካባቢዎች ትምህርት የሚሰጥ ነው:: በድርቅ በሚታወቀው አካባቢ የስንዴ ምርት ማምረት እንዲቻል ተደርጓል:: ለዚህ ደግሞ የትንበያ መረጃ ወሳኝ ሚና አለው:: በዚህ በኩል በተሰራው ስራም ድርቁን በዘላቂነት መቋቋም የሚያስችሉ እርምጃዎችም ተወስደዋል::

**አዲስ ዘመን፡- በተቋሙ የቦረናን ድርቅ ጨምሮ የመሬት መንሸራተት፤ ጎርፍ የመሳሰሉ አደጋዎች በሰው ሕይወት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መቀነስ እንዲያስችል የተንበያ መረጃ ተሰጥቶ ነበር?**

**አቶ ፈጠነ፡-** አዎ፤ ድርቅ ከመከሰቱ በፊት በነበረው መስከረም ወር ላይ ሁሉም ባለድርሻ ተቋም አስፈላጊውን ጥንቃቄና እርምጃ መውሰድ እንዲችል ምክረ ሀሳብና የትንበያ መረጃዎችን ሰጥተናል:: የትንበያ መረጃ እጥረት አልነበረም፤ ሆኖም በምክረ ሀሳቡ ልክ እርምጃ አልተወሰደም:: ለምን የሚለውን፣ የሚመለከትን ተቋም መጠየቅ ይገባል:: ከአየር ጠባይ ትንበያ አኳያ ግን መረጃ ቀድሞ ተሰጥቷል::

ይህ ብቻ ሳይሆን የትንበያ መረጃዎች ለአምስት ተከታታይ ወቅቶች በኢትዮጵያ አቆጣጠር ለሁለት ዓመት ስድስት ወር የሚሆን የአየር ጠባይ ትንበያ መረጃ ቀድሞ ይሰጣል:: ይሄን መነሻ ያደረገ ስራ እንዲከናወን ያስችላል:: ለምሳሌ፣ በቦረና ድርቅ ከሌሎች አካባቢዎች የሚገኝ የግጦሽ ሳርና መኖ ወደ ቦታው እንዲወሰድ በማድረግ እንስሳትን መታደግ ተችሏል:: ከዚህ ውጭ ከትንበያ መረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ምንም ክፍተት አልነበረም::

**አዲስ ዘመን፡- ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት ባህላችሁስ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ችግሮችን ለመቅረፍ ዓላማ ያደረገ የተጠናና የታተመ ሰነድ እንዲኖር አድርገናል:: የኢትዮጵያ የሜትሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥ ምን ይመስላል? የሚል (baseline assessment survey) የሚል ጥናት በገለልተኛ ወገን ተሰርቶ እንዲቀርብ ተደርጓል:: የተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ ምን እንደሚመስል ከተተነተነ በኋላ፤ ሌሎች ተቋማት የአጠቃቀምና የግንዛቤ እጥረታቸው ምንድ ነው የሚመስለው? የሚለው ተንትነናል:: ችግሮችን እንዴት እንፍታ? የሚል የ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ተሰርቷል:: ይህም የተቋሙ ሳይሆን ከግብርና፤ ውሃ እና ጤና ተቋማቱ ጋር በመሆን ብሔራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎት (national framework) የሚል ስራ ተሰርቶ፤ ክፍተቶች፤ እድሎችና ስጋቶች እንዲለዩ ተደርጓል::

የተነደፈውን እቅድ በብሔራዊ፤ በክልል ደረጃ፤ በዞን ደረጃ እንዴት እንተግብር የሚል የቅንጅት መመሪያ (cordination guideline) ተዘጋጅቷል:: ይህ እንዲተገበር ባለድርሻ አካላት ፈርመው አጽድቀዋል:: ስለዚህ የቅንጅት፤ የትብብርና የመተጋገዝ ጉዳይ ምላሽ ያገኘ ነው:: ሁሉንም በንቃት በመከታተል ባለሙያዎቻቸው መድበው እኛ ጋር ሰርተው እንዲቀርቡ ይደረጋል:: የተጠና የተሰነደ መረጃ ላይ የተመሰረተ ስራ እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ ዘመናዊ የሜትሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ከመጠቀም አንጻር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የዓለም የሜትሮሎጂ ድርጅት የወሰነው የመረጃ መሰብሰቢያ ስታንዳርድ አለ:: በዚህ ሁኔታ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው የሜትሮሎጂ ጣቢያዎች አሉ:: ሳይኖቲክ ተብለው የሚጠሩ አሉ:: እነዚህ በዓለም አቀፉ ስታንዳርድ መሰረት በየሶስት ሰዓት ልዩነት መረጃዎች ይሰበሰቡና ወደ መረጃ ቋት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## ‹‹ ከየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ በ15 ደቂቃ ልዩነት ውስጥ…

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

ይልካሉ:: ሁለተኛ ሶስተኛና አራተኛ ደረጃ የሚባሉም አሉ:: ሶስተኛ ደረጃ ዝናብና ሙቀት ብቻ የሚለካ፤ አራተኛ ደረጃ ዝናብ ብቻ ሚለኩ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎች አሉ:: እነዚህ መረጃዎች ከየጣቢያዎቹ ተሰብስበው ለውሳኔ ሰጭ አካላት ይተነተናሉ፤ ይሰነዳሉ:: ለምርምርም አጋዥ ናቸው::

አሁን ላይ ጊዜው የዲጂታል ዘመን እየሆነ ስለመጣ ከዚህ ጋር ተያይዞ ወደ አውቶማቲክ የአየር ጸባይ ጣቢያ እየተቀየሩ ነው:: ሰው አልባ የሆነ አውቶማቲክ የአየር ጸባይ ሁኔታ መከታተያ ጣቢያዎች 300 ደርሰዋል:: ከየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ በ15 ደቂቃ ልዩነት ውስጥ መረጃዎችን በሞባይል ሲም ካርድ ወደ ማዕከል ማስገባት የሚያስችል ስርዓት ተፈጥሯል:: ይህም ዋና ጠቀሜታው በጦርነት በተጎዳ አካባቢ፤ ሰዎች በአካል ሂደው መረጃ መሰብሰብ ባልቻሉባቸው አካባቢዎች ከማዕከሉ ሰርቨር ላይ ማግኘት ይችላሉ::

አውቶማቲክ የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር በ250 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ያለውን መረጃ ለመሰብሰብ ያግዛል:: በተለይ ለጎርፍ፤ ለድርቅ አስፈላጊ መረጃዎችን የሚይዝ ነው:: ይህ ራዳር ሻውራ ላይ አለ:: በቅርቡም ሰሜን ሸዋ ዞን እነዋሪ ላይ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ከፍታን መሰረት ያደረገ የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር የመትከል ስራ ተሰርቷል:: በሀዲያ ዞንና በቡኖ በደሌ ላይ በተመሳሳይ ተከላ ላይ ነው::

ይህ ራዳር በጣም ውድ ነው ነገር ግን የሜትሪዮሎጂ መረጃ ከማዘመን አንጻር ከፍተኛ ሚና አለው:: ሌላው የሳተላይት መረጃ ሲሆን ጣቢያዎቹ በሌሉባቸው አካባቢዎች ከሳተላይት የተቀዳ መረጃን በመጠቀም መረጃን መተንተን የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ኢትዮጵያ የዓለም የሜትሮሎጂ ድርጅት የስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት አባል ናት:: ኢትዮጵያ የዓለም ሜትሮሎጂ ድርጅት የአፍሪካ አህጉርን በፕሬዚዳንትነት እየመራች ነው::

**አዲስ ዘመን፡- መረጃዎችን ከመሰነድ እና ከማስቀመጥ እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ግብአት እንዲሆኑ ከማስቻል አኳያ በተቋሙ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እዚህ ሀገር ውስጥ የተደራጀ መረጃ ሊኖር የሚችለው የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ውስጥ ነው:: ጥሩ እና በተደራጀ መልኩ «በሃርድ ኮፒ» እና «በሶፍት ኮፒ» መረጃዎችን አደራጅተን እናስቀምጣለን:: <<የሃርድ ኮፒው>> መረጃው ላይ ድንገት እሳት ቢነሳ ወይም ጦርነት ተነስቶ ቢወድም «ዳታ ሪስኪዩ» ወይም ዳታን ከአደጋ መከላከል በሚል በዲጂታል መንገድ መረጃዎችን እናስቀምጣለን::

የተጠቃሚዎች የመረጃ አጠቃቀም ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ ነው:: ይሄ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ማንኛውም የዩኒቨርሲቲ ተመራቂ የሜትሮሎጂ መረጃ ሳያመጣ የዲግሪ ማሟያ ጽሁፉን ሊያስገባ አይችልም:: በማስተርስ እና በዶክትሬት ደረጃ ለጽሁፍ ማሟያቸው የሚጽፉት የኛን መረጃ ይዘው ነው:: በተጨማሪም የኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ እና ዓመታዊ የዝናብ መጠን በእያንዳንዱ ዘርፍ ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድ ነው የሚመስለው? የሚለውን ለማወቅ የሜትሮሎጂ መረጃን ሳይጠቀም ማስቀመጥ አይቻልም:: ተቋማት መረጃዎቻችንን ለምርምር ይጠቀሙበታል:: መረጃው በጣም ወሳኝነት ያለው ስለሆነ ተጠቃሚውም በዛው ልክ እያደገ ነው::

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ሰራተኞችም እድገት የሚያገኙት ምርምር በሰሩ ቁጥር ነው:: ተቋሙ የምርምር ተቋምም እየሆነ ነው:: ኢንስቲትዩት የሚለው የምርምር ተቋም እና የአቅም ግንባታ ተቋም መሆኑን የሚሳይ ነው:: ስለዚህ አንድ ሰራተኛ ከአንድ የስራ እርከን ወደ ሌላኛው መሸጋገር የሚችለው በሚያቀርበው የጥናት እና የምርምር ውጤት መሰረት ነው:: አንድ ሰራተኛ አንድ ግዜ ያደገበት የምርምር ስራ ውጤቱ ለሌላ ግዜ እድገት ለማግኘት ስለማይሆን ሰራተኞች «ሰርቫይቭ» ለማድረግ ሲሉ ምርምሮችን ያደርጋሉ:: እነዚህ የምርምር ስራዎች በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ፤ በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ሶሳይቲ (ማህበር) እና በኢንተርናሽናል ጆርናሎች ላይ ይታተማሉ:: ይሄም መነሳሳትን ይፈጥራል::

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቶቹ በተጨባጭ መፍትሄ ከማምጣት እና አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት ትንበያዎችን ከመስጠትስ አኳያ ያላቸው ጠቀሜታ ምን ይመስላል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት አለ:: ምርምሮቹ ውጤት እያመጡ ናቸው:: ከተቋማት ጋር በጋራ በመሆን የሚሰሩ ጥናቶች አሉ:: ጥናቶቹም ችግር ፈች መሆን አለባቸው:: የተለያዩ ዲፓርትመንቶች አሉን:: ለምሳሌ የትንበያ እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚባል አለ:: ይሄ ክፍል ሳይንሱን መሰረት አድርጎ፤ የ«ኢሊኒኖ» ተጽኖ፤ የ«ላኒናን» ተጽእኖ፤ የ«አረቢያን ሲ» በኢትዮጵያ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ በመውሰድ በራሱ ደረቁ ሳይንስ ላይ ጥናት ያደርጋል::

ሁለተኛ የሚመጣው ተጽእኖው በዘርፎች ይለያል:: በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊ፤ በውሃ፤ በግብርና እና በጤና ላይ ምን ተጽእኖ አለው? ግብርናም እንዲሁ ለብቻው በበቆሎ፤ በማሽላ፤ በአተር፤ በቅባት እህሎች እና በጥራጥሬዎች ላይ ያለው ተጽእኖ ለማወቅ ከተለያዩ አካባቢዎች ባሉ ማዕከላት እና ዋና መስሪያ ቤት ላይ ያሉ መረጃዎችን በመጠቀም ጥናትና ምርምሮች ይካሄዳል:: እነዚህ የምርምር ውጤቶች ለባለድርሻ አካላት እየቀረቡ ይተነተናሉ:: ስለዚህ በሚቀርበው ምክረ ሃሳብ መሰረት የበለጠ ዋናው ግቡ የትንበያውን እና የተጽእኖ ተጋላጭነት መጠኑን የሚቀንስ ጥናትና ምርምር ይደረጋል::

**አዲስ ዘመን፡- የመሬት መንሸራተት ጉዳይ ላይ ምን ያህል ጥናቶችን ትሰራላችሁ? ቅድመ ትንበያስ ትሰጣላችሁ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** «የላንድ ስላይድ» ጉዳዩን በተመለከተ በተቋም ደረጃ ኃላፊነቱ የኛ አይደለም:: ተቋማት የተቋቋሙለት ዓላማ አለ:: የሜትሮሎጂ መረጃ ሲባል ከገጸ ምድር በታች አንድ ሜትር ጀምሮ እስከ ከፍታ ውስጥ 30 ኪሎ ሜትር ያሉትን መረጃ የሚያጠቃልል ነው:: ከአንድ ሜትር በታች የሆነ ጉዳይ ከሆነ የኛ ጉዳይ ሳይሆን የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ጉዳይ ነው:: እኛ ከመሬት አንድ ሜትር ወደ ውስጥ የምንሰራው የአፈሩን «ቴምፕሬቸር» እና የእርጥበት መጠኑን መረጃ እንሰበስባለን:: ይሄ ለአስፓልት ስራዎችም ጠቃሚ ነው::

ከዛ ያለፈ ደግሞ «ከቮልካኒክ ኢራብሽን»ጋር፤ «ላንድ ስላይድ» እና ከመሬት መንቀጥቀጥ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በዋናነት ይሰራል:: ምክንያቱም ለዚህ ተቋም ያስፈልጋል:: ጃፓንም ውስጥ የሲስሞሎጂ እና ጂኦሎጂ ተብሎ አንድ ላይ ነው:: ኮሪያ እና ቻይና አደረጃጀታቸው ተመሳሳይ ነው:: ከኛ ሀገር አንጻር ሁሉን መረጃ አይደለም የምንከታተለው እኛ የምንከታተለው ከአየር ሁኔታ ጸባይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነው::

የሰው ሰራሽ አደጋዎች ማለትም በግጭት እና በጦርነቶች የሚነሱትን መተንበይ አንችልም:: እንደ ዜጋ ይመለከተናል ግን ዋና ስራችን አይደለም:: ዋና ስራው የሆነ ሌላ ተቋም አለ:: ስለዚህ የነዚህን ጥልቅ መረጃ የምናገኘው ከጂኦሎጂካል ሰርቬይ ነው:: ተቋሙ ካለ የምመክረው (ሪኮመንድ የማደርገው) በአዋጅ እና በስልጣን ሲሰጥ ለዛ የሚያስፈልገውን ባለሙያ ጭምር ማደራጀት ያስፈልጋል:: አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የተለያዩ ባለሙያዎች አሉት:: የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎችንም አካቶ አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል:: እኛ ግን የምናተኩረው ከአየር ጸባይ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ጉዳዮችን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- መረጃ ከሰጣችሁ በኋላ ሰዎች መረጃውን እየተጠቀሙበት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ትገመግማላችሁ? ከሆነስ ውጤቱን በምን መንገድ ትከታተላላችሁ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ባልተሰጠኝ ስልጣንና ኃላፊነት ውስጥ ይሄ ነው ማለት አልችልም:: ጦርነት እና የሰዎች መፈናቀልም አደጋ ነው:: በዋናነት የሜትሮሎጂ ስራ ሊሆን ግን አይችልም:: አደጋ መከላከል የሰብአዊ ድጋፍን ከማቅረብ አንጻር ተጎጂዎችን ለይቶ ከማገዝ ጋር ስራውን ሊሰራ ይችላል:: ሜትሮሎጂ ደግሞ በጦርነት ምክንያት የተፈናቀለ ሰው ቢኖር መጠለያ ከሌለው ዝናብ እየመጣ ነው ወይም ድርቅ አለ የሚለውን በመንገር መንግስት ዝግጅት እንዲያደርግ ምክረ ሃሳብ ይሰጣል::

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚባለው የምርምር እና አገልግሎት ሰጭ ተቋም ነው:: ባለስልጣን የተባሉት ደግሞ ተቆጣጣሪ ናቸው:: ለምሳሌ የሲቪል አቬሽን ባለስልጣን የአየር መንገዱ እና የኢትዮጵያ የሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት፤ የዓለም ሜትሮሎጂ ድርጅት አሰራርን እና የዓለማቀፍ የሲቪል አቬሽን አሰራርን ተከትለው መስራታቸውን ያረጋግጣል:: ከዛ ያነሰ ስታንዳርድ እየሰጡ ከሆነ የመቅጣት እና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት::

እኛ ግን የምንሰጠው አዋጁ ላይም የተቀመጠው አገልግሎት ነው:: አገልግሎት መስጠት ሲባል ለጤና፤ ለውሃ እና ለግብርና ሴክተሮች እንዲጠቀሙ ምክረ ሃሳብ እንሰጣለን:: ሴክተሮቹም የኛን መረጃ እና ትንበያ መጠቀም ይፈልጋሉ:: ስለዚህ ስለተቆጣጠርናቸው፤ ለምን አልተጠቀማችሁም ስላልናቸው ወይም ስላሰርናቸው ሳይሆን «ሰርቫይቭ» ለማድረግና የተሻለ ምርት እንዲኖራቸው ሲሉ የሜትሮሎጂ መረጃን መጠቀም ግዴታ ነው::

ግብርና ላይ ያሉት የአግሮ ሜትሮሎጂ ምክረ ሃሳብን ማግኘት አለባቸው:: መቼ ልዝራ? መቼ ልጨድ? መቼ መኸር ይሰብሰብ? የሚለውን ለመለየት መረጃ ይወስዳል:: ማዳበሪያ የሚወስደው ስላስገደድነው አይደለም:: ሕብረተሰቡም ስለሚያስፈልገው ነው:: ይሄም መረጃ እንደ አንድ ግብአት ስለሆነ መረጃውን ይጠቀማል:: እኛም ይሄንን አልፈን አስገዳጅ አላደረግነውም:: በየግዜው የምናካሂደው ግምገማዎችም የባለፈው የሰጠነው ትንበያ ምን ይመስላል? ምን ያህል ጠቅሞናል? ምንስ የጎደለ ነገር አለው? ምን መሟላት አለበት? የሚለውን በስፋት አንስተን እንገመግማለን:: ባለድርሻ አካላት ላይ የሚነሳ ክፍተት ካለ በዛው መድረክ ላይ ምክረ ሀሳቦችን እንሰጣለን::

**አዲስ ዘመን፡- ምክረ ሃሳብ የምታቀርቡበት የግዜ ገደብ አለ? ወይስ አደጋዎች ሲከሰቱ ነው ምክረ ሃሰብ የምታቀርቡት?**

**አቶ ፈጠነ፡-** በየሳምንቱ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዚዳንት ጀምሮ እስከ ሚዲያ አካላት ድረስ በየቀኑ መረጃ ያገኛል:: ለፕሬዚዳንቱ በየእለቱ ተፈርሞ መረጃው በ«ሃርድ ኮፒ» ይገባል:: ለግብርና ሚኒስቴር እና ለመከላከያ መረጃው ይሰጣል:: ይሄም የሚደረገው አደጋ ካለ ሰዎችን ለማውጣት እንዲቻል ነው::

የአጭር ግዜ፤ የመካከለኛ እና የረጅም ግዜ በመባል የምንሰጠው ትንበያ በሶስት ይከፈላል:: የአጭር ግዜው ቅጽበታዊ ጎርፍ በሚከሰትበት ወቅት የሚያገለግል ነው:: መካከለኛ ግዜ የሚባለው እስከ 10 ቀን ያሉትን ለውሳኔ ሰጭ አካላት ምን እንደሚመስል መረጃ የምንሰጥበት ነው:: ከሶስት እስከ አራት ገጽ የሆነ ምክረ ሃሳብም እንሰጥበታለን::

በየሴክተሩ ደግሞ ፕላትፎርም አለ:: የአግሮ ሜትሮሎጂ ግብረኃይል አለ፤ የውሃ ሜትሮሎጂ (ሀይድሮ ሜትሮሎጂ) እና ከጤና ጋርም ራሱን የቻለ ግብረ ኃይል አለ:: እነዚህ ዘርፎች ራሳቸውን የቻሉ ፕላትፎርም አላቸው:: በዛም መረጃ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ:: ክልሎችም እንዲሁ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል በኦሮሚኛ ለሁሉም ለሚመለከታቸው ተቋማት መረጃ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ:: ውሳኔ ሰጭው ደግሞ በሃገሪቱ ውስጥ ያለው የአየር ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚለውን በየ10 ቀናት ውስጥ መረጃው በቢሯቸው ይገባል:: ስለዚህ ወቅት ጠብቀን አይደለም መረጃ የምንለዋወጠው::

በግብርና ስራ ውስጥ የሚዘራ ነገር ስላለ የአጭር ግዜ ትንበያ አይደለም የሚስፈልገው የረጅም ግዜው ነው:: የዝናቡ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚለውን ቅድመ ጥቆማ እንሰጣለን:: አምስት ወር ቀድመን የበልግ ትንበያ እንሰጣለን:: ውሃ የሚያዝ ከሆነ ለመያዝ እንዲያመች በአጠቃላይ ለአደጋ ተጋላጭ የሆነ ሁኔታ ካለ ቀድመን እርምጃ ለመውሰድ የሚስችለን መረጃ የምንሰጥበት ነው::

አቬሽንን ብንወስድ ቀን ተጠብቆ ሳይሆን በየሰዓቱ መረጃ ይሰጣል:: አውሮፕላን ሲነሳ፤ ሲጓዝ እና ሲያርፍ መረጃ እንሰጣለን:: ይሄንን መረጃ በመጠቀምም አውሮፕላኑ ለመነሳት ይዘገያል? ወይም አይዘገይም? የሚለውን እና ለማረፍም የአየሩን ሁኔታ እናሳውቃለን:: አየሩ የማያሳርፍ ከሆነ እስኪከፍት ድረስ ካለበት አይነሳም ወይም ሰማይ ላይ የሚሽከረከርበት እና ወደ አቅራቢያው ባለው ኤርፖርት የሚያርፍበት ሁኔታ ካለ እናሳውቃለን:: ስለዚህ ይሄን አይነቱ የመረጃ ልውውጥ በሰዓታት ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- በስራችሁ ሂደት እንቅፋት ወይም ተግዳሮት የሆኑባችሁ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ችግሮች ወደ እድል ከመቀየር አኳያስ ምን ሰራችሁ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እንደማንኛም ስራ ከየትኛውም ዩንቨርሲቲ የተመረቀ የሰው ኃይል አይደለም የምንወስደው:: ሙያው ልዩ ትኩረትን ይፈልጋል:: ተቋሙ በአብዛኛው በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል ከማቆየት አንጻር ውስንነት ነበረው:: ብዙዎቹ ወደ ሌሎች ግብርና እና ሌሎች ተቋማት ላይ የመስራት እድል አላቸው::

ከአቬሽን ጋር አብረን እንሰራለን:: የአየር በረራ ስኬታማ የሚያደርጉት የአቬሽን ሜትሮሎጂ የሚባል ዲፓርትመንት አለ:: ካሉን ሰራተኞች እና በጀት አንጻር ወደ አንድ ሶስተኛ የሚሆነው ለዚህ ዲፓርትመንት ነው የምናውለው::

አየር መንገዱ የተሳካ በረራ እንዲያደርግ የእኛም ድርሻ አለበት ብለን እናምናለን:: ለኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ ስኬታማነት በርካታ ተቋማት ሚና አላቸው:: ሜትሮሎጂ አንዱ እና ዋናው ነው:: የትኛውም አውሮፕላን የሜትሮሎጂ መረጃ ሳያገኝ መነሳት፤ መብረር እና ማረፍ አይችልም:: ዓለማቀፍ ሕጉም ያስገድደዋል:: መረጃ ሳያገኝ ምናልባት ተነስቶ አደጋ ቢመጣ የኢንሹራንስ ተቋማቱ ካሳውን ለመክፈልም ይቸገራሉ::

የእኛ ተቋም ከዛሬ አምስት ስድስት ዓመት በፊት የሰው ኃይል ችግር ነበር:: ከጥቅማ ጥቅም እና ከክፍያ አኳያ ቅሬታም ነበራቸው:: በዛም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራተኛም ይለቃል:: ይሄንን በመያዝም የሰው ኃይል ሃብታችን ላይ በቁርጠኝነት መስራት ነበረብን:: በዚህም በአጭር ግዜ ውስጥ ወደ 121 የሚሆኑ ተመራማሪዎችን በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ማስመረቅ ተችሏል::

ከአርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ ጋር በመስማማት በሌሎችም ዩኒቨርሲቲዎች፤ «የክላይሜት ሪሌትድ ሰርቪስ» ከሚሰጡ ተቋማት ጋር እና ከዓለም ሜትሮሎጂ ድርጅት ጋር እንዲሁ በሕብረት በመስራት የሚሰጡንን እድሎች በመጠቀም በቻይና እና በአሜሪካ ከሚገኘው ተቋም ጋር በመነጋገር ጅግጅጋ፤ ሀዋሳ እና አዲስ አበባ ላሉ ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ አድርገናል:: ችግሮችም የተቀረፉበት ሁኔታ አለ:: የሜትሮሎጂ ተጨባጭነትም ጨምሯል::

መንግስትም ለጉዳዩ ትኩረት የሰጠበት እና የዓለም ሜትሮሎጂ ድርጅት ጋር በመነጋገር የአፍሪካ የሜትሮሎጂ ጽህፈት ቤቱ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሆን ማድረግ ችለናል:: ይሄንን ለማድረግም ከብዙ ሀገራት ጥያቄውን አቅርበው ስለነበር እኛ በቀኝ ገዥዎች ያልተገዛን መሆናችንን፤ ተቋሙ በየግዜው እያደገ ያለ መሆኑን እና የኢትዮጵያ አየር መንገድም በሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ላይ በረራ ያለው መሆኑን በማስረዳት ጽህፈት ቤቱ እዚሁ እንዲሆን ማድረግ ችለናል:: ስለዚህ ያጋጠሙንን ችግሮች ወደ እድል መቀየር ችለናል::

**አዲስ አበባ፡- ተቋሙ በቀጣይ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመር ጭምር ለመስራት ምን አቅጣጫ አስቀምጧል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ዋናው መዘመን ነው:: በሆነ ግዜ አንድም ራዳር አልነበረንም በቅርብ ወደ አራት ተክለናል:: ዋጋው ውድ ስለሆነ እንጂ ለኢትዮጵያ አራት ራደር ብቻ በቂ አይደለም:: በስቴሽን ማስተር ፕላናችን መሰረት 12 ራዳር ያስፈልገናል:: ስለዚህ ገና ስምንት ያስፈልገናል:: ለዚህ ደግሞ ሃብት የማፈላለግ ስራ ይጠበቅብናል:: ዓለም አቀፍ የመረጃ ልውውጥንም የማጠናከር ስራ መስራት አለብን:: ይሄንንም ታሳቢ በማድረግ የሃብት ማፈላለግ ስራ እየተሰራ ነው:: በአብዛኛው ሀገራችን የተሳካላት ሀገር ናት:: በጣም ውስን የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ በቅርቡ ኢትዮጵያ አንዷ ሆና ሪሶርስ ያገኘንበት ሁኔታ አለ::

ለአውሮፕላን በረራ የሚደረገው የሜትሮሎጂ ትንበያ መሳሪያውን ራሱ አውሮፕላኑ ላይ መግጠም እና አውሮፕላኑ በሚበርበት ከፍታ ልክ መረጃ እየሰበሰበ እንዲልክልን በማድረግ እና በመተንተን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በደረሰባቸው ቦታዎች ሁሉ መረጃ ሰብስቦ የሚመጣልንን ሁኔታ ለመፍጠር በትኩረት እየሰራን ነው:: በአጠቃላይ በአስቀመጥነው ራዕይ መሰረት የሜትሮሎጂ መረጃዎችን የሚያዘምን ስራ ይሰራል::

ሌላኛው፣ የዓለም ሜትሮሎጂ የአፍሪካ ጽህፈት ቤት መቀመጫው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሆን ማድረግ ችለናል:: ለዚህም ቦሌ ላይ እየገነባን ያለነው ሕንጻ «የካፓሲቲ ቢዩልዲንግና» የምርምር ተቋም ነው:: ይህ ማለት በአብዛኛው የአፍሪካ ተቋማት «የሪጂናል ትሬዲንግ ሴንተርን» በማጠናከር ለሌሎች የአፍሪካ ወንድሞቻችን አገልግሎት በመስጠት ከዓለም ሜትሮሎጂ የሚገኘውን አቅም በመውሰድና በራሳችን ያለንን አቅም በማጠናከር ታዋቂ የሜትሮሎጂ ሴንተር እንዲሆን ለማድረግ እየተሰራ ነው::

አንዱ የሜትሮሎጂ የልህቀት ማዕከል እንዲሆን ለማድረግ ከዓለም የሜትሮሎጂ ድርጅት ጋር እና ከአፍሪካ ጽህፈት ቤት ጋር መግባባት ላይ ደርሰናል:: አንዱ የሜትሮሎጂ መረጃ በመጠቀም ምርት እና ምርታማነትን የማረጋገጥ፤ ከአደጋ ተጋላጭነት ስጋት ነጻ የሆነ ማህበረሰብን የማየት ሕልም ይዘን እየሰራን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም ቀረ የሚሉት እና የሚያስተላልፉት ሀሳብ ካለ እድሉን ልስጥዎ!**

**አቶ ፈጠነ፡-** ሚዛኑን የጠበቀ የአየር ንብረት እንዲኖረን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብራችንን አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል:: በሀገራችን የዝናብ መጠናችንን ለመጨመርና የውሃ ምንጮቻችንን ለማጎልበት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብራችንን ማጠናከር ያስፈልጋል:: በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመሩ ስራዎችን መንከባከብና በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ጠቃሚ ይሆናል:: ሕብረተሰቡም ይሄንን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል:: በተቋም የሚሰጡ ትንበያዎችን በመጠቀም የመኸር እና የመስኖ ስራዎችን በማጠናከር የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ያስፈልጋል::

የኮሊደር ልማቶቹም የጎርፍ አደጋዎችን ለመከላከል ሚና ይኖራቸዋል:: ለምሳሌ በአዲስ አበባ የውሃ ማፋሰሻ ቦዮች ችግር ነበረባቸው:: አሁን የተጀመረው ኮሊደር ስራ በከተሞች ላይ የሚፈጠረውን የጎርፍ አደጋ ለመቀነስ ሚና አለው:: በገጠር አካባቢዎች እና በረባዳማ ቦታዎች ላይ እንዲሁ ለሚከሰቱ የጎርፍ እና የመሬት መንሸራተቶች ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ከወዲሁ የአሰፋፈር ሁኔታዎችን ማስተካከል ተገቢ ስለሆነ ዝግጅት ቢደርግበት መልካም ነው::

አርብቶ አደሩ እና አርሶ አደሩ የሚሰጡ ትንበያዎችን በመመልከት በመኸር ግዜ የሚፈጠረውን ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብን በሚመለከት የሚሰጡ ምክረ ሀሳቦችን በመስማት እርምጃ መውሰድ እንዲችል መልእክቴን አስተላልፋለሁ:: እነዚህን አጠናክረን ከቀጠልን ሀገራችን የጀመረችውን የልማት ጉዞ ማስቀጠል እንችላለን::

**አዲስ ዘመን፡- ለጊዜዎትም ለሀሳቦትም አመሰግናለሁ!**

**አቶ ፈጠነ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ካለንበት ሰጣ ገባ ወጥተን ለሁላችንም ወደሚበጅ የሰላም አንባ ለመድረስ

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

ትላንት ብለን በምናስታውሳቸው ሀምሳ ዓመታት ውስጥ እንደ ሀገር ሰላም ናፋቂ ህዝቦች ሆነናል:: ለመነጋገር እና ተነጋግሮም ለመደማመጥ የሚያስችል ማህበረሰባዊ ስሪት ማጣታችን ፤ሀይልን ባስቀደመ የፖለቲካ እሳቤ ፖለቲከኞች መቃኘታቸው ፣ ከዛም አልፎ ለእርስ በርስ ግጭቶች መንገድ የሚከፍቱ የጥላቻ ትርክቶች በዝተው መደመጣቸው ሰላምን ነፋቂ አድርገውናል::

በዚህ ጽሁፍ ዓላማ ያደረኩት "እርቅ ደም ያደርቅ" የሚለውን የአባቶች አነጋገር መሰረት በማድረግ፤ መጪዎቹን ዘመናችንን ብሩህ ማድረግ እንደምንችል ለማሳየት ነው:: በእርቅ ቁርሾዎቻችንን ሳናክም እንደበጎ ውርስ ሞትና ጦርነትን ለትውልዱ ማውረስ እንደሌለብን ለማመላከት ነው::

ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ሆን ተብለውም ይሁን ባለማወቅ የተፈጠሩ አራራቂና አቀያያሚ ትርክቶች ተስተካክለው እንደብሔር ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያዊ፣ እንደባዕድ ሳይሆን እንደወንድማማች የምንተያይበትን የሰላም አውድ መፍጠር የዚህ ዘመን ትውልድ ኃላፊነት ነው::

አሁን ላይ በእርቅ እና በምክክር ወንድማማችነታችንን እንመልስ ብለን ስንነሳ ትውልዱን በእልህ ሳይሆን በይቅርታ ሰላምን ማምጣት እንደሚችል በማስተማር ነው:: በምክክርና በውይይት ካልሆነ በሀምሳ ዓመታት የፖለቲካ ትንቅንቅ ውስጥ ሰብተውና ደልበው የፈረጠሙ የዘረኝነት፣ የጦርነትና የጥላቻ መንፈሶቻችንን ማስወጣት አንችልም::

ጊዜም በውይይት ካልሆነ በሌላ በምንም መንገድ ሰላምን ማምጣት እንዳንችል የሆንበት ነው:: ከምክክር ውጪ ምንም ማድረግ በማንችልበት ዘመን ላይ በጦርነት ዋጋ መክፈል ከምንም የማይወዳደር ራስ ጠልነት ነው:: ለራሳችን ክብርና ዋጋ ከምንሰጥበት አጋጣሚ አንዱ ጦርነትን በውይይት፣ ጥላቻን በፍቅር ማስቀረት ነው::

ብዙሀኑ ሀገራት ራሳቸውን በመውደድና በማፍቀር ጨርቃቸውን የጣሉ ናቸው:: እኛ ግን ለማንም ትርፍ በማያስገኝ ጦርነት ውድ ህይወታችንን እናጣለን:: ለብዙ ዓመታት የለፋንበትን ንብረታችንን እናወድማለን:: ጦርነት ለማንም ድል አስገኝቶ አያውቅም:: አክራሪ እና ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ማንንም ፊተኛ አድርገው አያውቁም::

ፊተኝነትና ብኩርና ያለው የጋራ እሳቤ በፈጠረው አብሮነት ውስጥ ነው:: ሀገራዊ ድል፣ ህዝባዊ ልዕልና ያለው ብዙሀነትን ባቀፈ የሰላምና የእርቅ መድረክ ላይ ነው:: የደበዘዙ የጋራ ጸዳሎቻችንን በማጥራት፣ የከሰሩ አስታራቂና አዋሃጅ እሴቶቻችን የአብሮነት መንገድን እንዲጠርጉልን ለእርቅ መቀመጥ ፍሬ የምናፈራበት የሰላም መንገዳችን ነው::

ጦርነት የሞት አዋጅ ነው:: በዚህ አዋጅ ውስጥ ሰላም አለ ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው:: ቀድሞውኑ ማንም ጠብቆ አያውቅም:: ወደጦርነት የሚሰማራ ሁሉ ለመግደልና ለመሞት ነው:: በምክክር ነገሮችን ማስተካከል እየተቻለ በሀገርና ትውልድ ላይ መርዝ ለመርጨት መሰናዳት መቼም ቢሆን አዋቂነት አይሆንም::

ጦርነት ውርስ ነው:: ዛሬ ላይ የሚያባራ አይደለም:: እንደሰደድ እሳት ወደነገ ርቆ የሚንጠራራ የሞት ቅርስ ነው:: ሰው እንዴት ሞትን ለትውልድ ያወርሳል? እንደምን መከራን ለመጪው ያስቀምጣል? ስለምን ጥላቻና በቀልን ለልጅ ልጆቹ ያስታቅፋል? ከትላንት በወረስነው የፖለቲካ ውርስ እየተሰቃየን እንዳለን ሁሉ ዛሬ ላይ በምንሆነው ነገር ለነገው ትውልድ መከራን እያስቀመጥንለት ነው::

ጦርነት ማለት ‹ነገን ዛሬ ላይ ቆሞ እንደማውደም› ነው:: እውነት ነው ነገን ዛሬ ላይ ማውደም ከመሆን ውጪ ምንም ሊሆን አይችልም:: ባደረግናቸው የእርስ በርስ ጦርነቶች ነጋችንን እያወደምን እንደሆነ እናውቃለን? ነገ ማለትስ ለኛ ምን ማለት ነው? ነገ ማለት ትውልድ ነው፣ ነገ ማለት የትውልድ ህልምና ራዕይ ያለበት፣ የሀገር ተስፋ የተቀመጠበት ካዝና ማለት ነው:: ዛሬ ላይ በእልህ ይህን ህልምና ተስፋ ካጠፋን ምን ነገ ይኖረናል?

**ሰላምን ለኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያን ለሰላም የሚለው መነሻ ሀሳቤ ሀገራችንን ከጦርነት የምንታደግበት፤ ትውልዱን ከጥላቻ፤ ፖለቲካውን ከአክራሪ እና ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ነጻ የምናወጣበት እንዲሁም ለአዲስ ህዝባዊ አስተሳሰብን የምንሰናዳበት የተሀድሶ ምእራፍ ነው**

ነገን ዛሬ እንስራ በሚል ሀገራዊ ንቅናቄ ውስጥ ብዙ ትግሎችን አድርገናል፤ አሁንም በዛ መሪ ሀሳብ ውስጥ በርካታ በጎ ህልሞችን እያለምን እንገኛለን:: ይህም ሆኖ ግን አክራሪ እና ጽንፈኛ አስተሳሰቦች በሚፈጥሯቸው ጦርነቶች ነገን እያወደምን ነው ። ዛሬ ላይ ይህንን እውነታ መረዳት ካልቻልን ችግሩ አብሮን መዝለቁ አይቀርም።

ነገ የዛሬ መልክ ነው፣ መጪው , የአሁን ጽንስ ነው..ዛሬ የምንሆነው ሁሉ ወደነገ የሚሄድ ነው:: በዚህ መልኩ ነገ አይሰራም:: ነገ የሚሰራው ሰላም ሰባኪ በሆኑ አንደበቶች፣ ለእርቅና ለአብሮነት በበረታ አዕምሮና ልብ በኩል ነው:: መጪው የሚቀናው ኢትዮጵያን ለሰላም ሰላምን ለኢትዮጵያ ስናሰናዳ ነው:: በትውልዱ መሀል ኢትዮጵያዊነት ሲጸና ነው:: በከረረ ፖለቲካ፣ በጠብ ጫሪ ንትርክ ነገ ይወድማል እንጂ አይሠራም::

እየሄድንበት ባለው ሰላም አልባ መንገድ ራሳችንን እየጎዳን ነው:: ሰላም እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን፤ ስለሰላም ብዙ ንግግሮችን እናደርጋለን፤ ለሰላም ዋጋ ስንከፍል ግን አንታይም:: ነገን ዛሬ እንስራ፤ ለትውልዱ ጥላቻን ሳይሆን ፍቅርን እናስቀምጥለት ስንል ህዝባዊ ንቅናቄ እናደርጋለን እንደሀሳባችን እውነት መር በሆነ ክዋኔ ስንሰለፍ አንታይም::

የሆነን የአንድ ዘመን ክብርና ማንነትን ነበር ብሎ ማውራት እጅግ ያማል:: ሰላም አጥተን፣ አንድነት ርቆን አሁን ላይ ነበር ብለን እያወራን ነው:: በሰላም ለሰላም የቆሙ ህዝቦች፣ በአንድነት ለአንድነት የተሰለፉ ልቦች ዛሬ በእኔነት ጠይመው እዛና እዚህ በቡዳኔ ቆመው ማየት ያማል::

ብዙሀነትን በአብሮነት ያጸኑ፣ በመከባበርና በመቻቻል ለዓለም ምሳሌ መሆን የቻሉ የይቅርታ ፈሮች ዛሬ በብሄር በልጽገው ኢትዮጵያዊነትን ሲሸሩት ማየት ያስቆጫል:: መልኮቻችንን ወደዛሬ መልሰን ዳግም የሰላም ህዝቦች ከመሆን ውጪ ትላንትን መዘከሩ ትርጉም አይኖረውም:: በውይይት ልዩነቶቻችንን አጥበን ነበር ብለን የምናወራውን ክብራችንን ወደዛሬ ማምጣት ይቻለናል::

ለዚህ አይነቱ ህዝባዊ መሻት ሀገራዊ ምክክር በሰፋና በገዘፈ የአብሮነት ዓላማ ዝግጅቱን አጠናቆ እየጠበቀን ነው:: ብሄራዊ ምክክርን ለብሄራዊ ተግባቦት በመጠቀም ሀገራችንን ነጻ ማውጣት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው:: ሜዳውና ፈረሱ ተዘጋጅቶልናል ጋላቢ መጠበቅ አይጠበቅብንም:: በላመና በላቀ አስታራቂና አቀራራቢ ሀሳብ ሰላም ለማውረድ ምቹ ሁኔታ ላይ እንገኛለን:: እድሎቻችን ፍሬ አፍርተው ድህነት እንዲሰጡን ለሁለንተናዊ እርቅ ይሁንታ ማሳየት ይጠበቅብናል::

ዓመታትን በወሰደ ቅድመ ዝግጅት መነሻውን ሀገር መድረሻውን አብሮነት አድርጎ የተጀመረው ብሄራዊ የእርቅ መድረክ በሀሳብ ፍጭት ኢትዮጵያን ሊታደግ እንሆ ደጃፉን ከፍቷል:: እንደሀገር የወደቁብንን የዘረኝነት ቀንበሮች ለማለዘብ፣ ነጣጣይ ትርክቶችን በብዙሀነት ለማከም ከፍ ሲልም በማይደገም ህዝባዊ እሳቤ ሀገር ለማጽናት እንዲህ አይነቱን አጋጣሚ ያለዋዛ መጠቀም ያስፈልጋል::

በየትኛውም የዓለም ክፍል ችግሮች ይፈጠራሉ የእኛን ሀገር ችግር ለየት የሚያደርገው ችግር የመፍጠራችንን ያክል መፍትሄ ለማምጣት አለመተባበራችን ነው:: እንዲህ አይነቱ ልምምድ የቆዩ ችግሮች በጊዜ መ መ ቆ ጨ ት ሲገባቸው አዲስ ችግሮችን እንዲፈጥሩ እድል በመስጠት የከፋ ችግር ሲያደርስ ቆይቷል::

የመጣንበት የኃይል አሰላለፍ ከጦርነት በኋላ ሰላምን አምኖ የተቀበለ ነው:: ከጦርነት በኋላ ሰላም ለማንም የማይበጅ፣ ብዙ ነገሮችን የሚያበላሽ ድርጊት ነው:: እየመከርን ያለነው ከጦርነት በፊት ሰላም እንዲመጣ፣ ሳንሞትና ሳንገዳደል በእርቅ ተግባቦትን ለመፍጠር ነው:: እየደከምን ያለነው ልዩነቶቻችን ሰፍተው እንዳያገፉፉን፣ በኃይል ሳይሆን በሀሳብ የበላይነት መሸነፍን ባህል ለማድረግ ነው::

ብኩርና ከህዝብ ጋር ተራምደው የሚደርሱበት እንጂ በአክራሪ እና ጽንፈኛ አስተሳሰቦች ተራምደው የሚደርሱበት አይደለም:: ማንም በነዚህ አስተሳሰቦች ተራምዶ ሩቅ አልደረሰም:: ማንም ለብቻው ተጉዞ ለክብር አልበቃም:: ትርፉችንና ክብራችን ያለው ሀገር በቀደመችበት ፖለቲካና ህልማችን በኩል ነው:: ወደኋላ የተጓዝነው ሀገር በሌለችበት የብቻ ሩጫ ትንቅንቅ ስለያዝን ነው:: የተገፋፋነው ብዙሀነት በሌለው እኔነት ውስጥ ስለጎለመስን ነው::

ጦርነት ለማንም መፍትሄ ሆኖ አያውቅም:: የትውልድ ተስፋና የሀገር ብልጽግና በሰላም እሳቤ ውስጥ የሚውለበለቡ ናቸው ሰንደቁን አፍርሶ ልማት የለም:: ዓርማውን አውርዶ ተስፋ የለም:: አስቀድመን በሰንደቁ ላይ የሰላም ዓርማን እንስቀል ያኔ ሁሉም ነገር መልካም ሲሆን እናያለን::

ሁሉም ነገር መልካም ያልሆነው ሰንደቁ ላይ ሰላም ስለሌለ ነው:: ሰንደቁ ላይ መከራና ሰቆቃን፣ ጦርነትና ዋይታን ሰቅለን እንዴት ነው ብርሀን የሚወጣልን? እንዴት ነው በሰማያችን ላይ ጨረቃ የምትፈነጥቀው? ብርሀን እንዲመጣ ወጀቡ ገለል ማለት አለበት፣ ጭጋጉ መጥራት ይኖርበታል::

ያለቅድመ ሁኔታ ሰላም ያስፈልገናል፣ አብሮነት ግድ ይለናል:: እንደሰላም ያሉ በሀገር ግንባታ ላይ የላቀ አስተዋጽኦ ያላቸው የትስስር ገመዶች በአንድ ወገን የሚጸኑ ሳይሆኑ የሁሉንም ሰው ትብብር የሚሹ ናቸው:: ብሔራዊ ምክክር የህዝብ ድምጽ የሚሰማበት፣ አብሮነት የሚጸናበት በስተመጨረሻም በአንድ አሸናፊ እውነት ኢትዮጵያዊነትን የምንገልጥበት የእርቅና የወዳጅነት መንፈስ ነው::

ሰላምን ለኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያን ለሰላም የሚለው መነሻ ሀሳቤ ሀገራችንን ከጦርነት የምንታደግበት፣ ትውልዱን ከጥላቻ፣ ፖለቲካውን ከአክራሪ እና ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ነጻ የምናወጣበት እንዲሁም ለአዲስ ህዝባዊ አስተሳሰብን የምንሰናዳበት የተሀድሶ ምእራፍ ነው:: በመጣንበት መንገድ መሄድ ሳይሆን አዲስ አቅጣጫ መቀየስ ይኖርብናል:: በሀሳብ የዳበረ፣ በውይይት የሰመረ፣ ትላንትን በይቅርታ የሻረ፣ ዛሬን በእርቅ የተቀበለ፣ መጪውን በተስፋ የሚቀበል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ብቻ የሚጠሩበት አቅጣጫ ያስፈልገናል::

ኋዳ የተደበቁ የጋራ እሴቶቻችን ወደአደባባይ ወጥተው ኢትዮጵያዊነትን ይናገሩ:: መካሪና አስታራቂ ሆነው ዘመናትን የቆዩ ትውፊቶቻችን ማን እንደነበርን፣ እንዴት እንደነበርን ጽኑ ፍቅራችንን ይመስክሩ:: በፖለቲካ ትርክት የጨቀዩ አብሮነትን የኳሉ የታሪክ ሰነዶቻችን ለወደቀብን ሀገራዊ መከራ መልስ እንዲሰጡን ወደኋላ መለስ እንበል:: በክፉዎች የተደበቁ ተሳስረንና ተጋምደን የመጣንባቸው ህብረ ቀለሞቻችን ማንነታችንን ይግለጡ:: የለበስናቸውን የዘር ካባዎች አውልቀን በጋራ የሰፋነውን የአብሮነት ሸማ ስንከናነብ ያን ጊዜ ነገሮች እንደምንፈልጋቸው መሆን ይጀምራሉ::

በሀሳብ በልጽገን በመከራዎቻችን ላይ የበላይ እስካልሆንን ድረስ፣ በሀሳብ በልጽገን የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር እስካልነቃን ድረስ ከምኞታችን አንደርስም:: ምኞት ምቹ ልብ ይፈልጋል:: ምቹ ልብ ደግሞ ሰላም ያለበት፣ በፍቅርና በይቅርታ የዳበረ ነው:: ካለሰላም የትኛውም ህልም ፍሬ ማፍራት አይችልም:: ካለእርቅ የትኛውም ዓላማ ግቡን መምታት አይሆንለትም:: ካለንበት ሰጣ ገባ ወጥተን ለሁላችንም ወደሚበጅ የሰላም አንባ ለመድረስ ተግባቦትን ተልዕኮው ላደረገ ውይይት ልባችንን ክፍት እናድርግ::

# የውስጥ አቅምን አሟጦ በመጠቀም ገቢን ማሳደግ የቻለው የሲዳማ ክልል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የሲዳማ ክልል በክልልነት ከተደራጀ ጊዜ ጀምሮ ባለፉት አራት ዓመታት የክልሉን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን በመመለስ ረገድ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሰራ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ:: የማህበረሰቡን የመልማት ጥያቄ ለመመለስ በተለይም ክልሉ ኢኮኖሚያዊ አቅሙ እንዲጎለብት ለማድረግ ከሰሯቸው ጠንካራ ሥራዎች መካከልም የውስጥ ገቢን ለማሳደግ የተከናወነው ተግባርና የተዘገበው ውጤት ይጠቀሳል::

የሲዳማ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አራርሶ ገረመው በተለይ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ባደረጉበት ወቅት እንዳሉት፤ ባለፉት አራት ዓመታት በተከናወነው ተግባር በተለይም የማህበረሰቡን የመልማት ጥያቄ ለመመለስ በርቱ ጥረት ተደርጓል:: ከእነዚህም መካከል የክልሉን ገቢ ማሳደግ አንዱና ዋነኛው ነው፤ በዚህ በኩል በተከናወነው ተግባር የውስጥ ገቢን በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ተችሏል::

ክልሉ ከዚህ ቀደም ይሰበስብ ከነበረው ሁለት ቢሊዮን ብር ዓመታዊ የውስጥ ገቢ እምቅ አቅሙን ወደ 13 ቢሊየን ብር አሳድጓል:: በተያዘው በጀት ዓመት ደግሞ አቅሙ አሟጦ በመጠቀም ወደ 13 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዷል:: ይህን ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው በአመራሩ ቁርጠኝነት ሲሆን፤ በዋናነት እዚህ ስኬት ላይ መድረስ የተቻለው በክልሉ ያለውን ውስን ሃብት በአግባቡ በመሰብሰብ፣ ብልሹ አሰራሮችን በመቀነስ፣ ሌብነትን በመጠየፍ በተሰራው ስራ ነው::

እሳቸው እንዳሉት፤ ክልሉ ዞን ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ የማዳበሪያ ዕዳን ጨምሮ የተለያዩ ውዝፍ ዕዳዎች ነበሩበት:: ይሁንና በተሰራው ጠንካራ የገቢ አሰባሰብ ሥራ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ ዕዳውን ሙሉ በሙሉ መክፈል የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዕዳ ሲከፈል የሚፈጠረውን ጎዶሎ በገቢ ለመሙላት ክልሉ ሰፊ ጥረት አድርጓል:: አመራሩ ሃብትን በአግባቡ ለመምራትና ለመጠቀም ባደረገው ብርቱ ጥረት እንዲሁም ከፋይናንስ አሰራር አንጻር በተለይም የፋይናንስ ስርዓቱን ገቢና ወጪውን በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር በዚህም የክልሉን ገቢ ትርጉም ባለው መንገድ ከፍ ማድረግ ተችሏል::

ገቢና ወጪ ተያያዥ ጉዳዮች ናቸው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ከፍተኛ የሆነው ሃብት ለግዢ እንደሚውል ገልጸዋል:: በዓመት ውስጥ ከሚመደበው በጀት ከ63 እስከ 64 በመቶ ያህሉ ለግዢ እንደሚውል ጠቅሰው፣ ግዢ የራሱ የሆነ ደንብና አሰራር እንዲሁም ግልጽ ጨረታ ያለው ቢሆንም በአግባቡ ካልተመራ በስተቀር ሾልከው የሚወጡና ሃብትን የሚያባክኑ ችግሮች ያጋጥሙታል ሲሉ አስታውቀዋል:: ክልሉ በአሁኑ ወቅት ሃብትን በመቆጠብ በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል ጥቅል ግዢን ተግባራዊ ማድረግ ችሏል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ለእዚህም የጎማ ግዢን ተግባራዊ በማድረግ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉንም ጠቅሰዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሁሉም ክልሎች ቀዳሚ በመሆን የመንግሥት ግዢን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማድረግ ወደ ስርዓቱ እየገባ ነው:: በአሁኑ ወቅት ክልሉ እንደ ክልል ጥቅል ወደሆነው የግዢ ስርዓት መግባት ችሏል:: በቅርቡም የጎማ ግዢን በጥቅል ግዢ መግዛት የቻለ ሲሆን፤ ይህም ወጪን በመቆጠብ፣ አስተማማኝነቱን በማረጋገጥና ሃብትን በመቆጠብ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል::

ጥቅል ግዢ የሃብት ብክነትን በእጅጉ የሚቀንስ ከመሆኑም ባለፈ አያጨናንቅም የሚሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የቁጥቁጥ ግዢ ሃብት እንደሚያባክን አመልክተዋል:: በቀጣይም ቁጥ ቁጥ ከሆነ ግዢ በመውጣት ሙሉ ለሙሉ ወደ ጥቅል ግዢ መግባት የቢሮው ዋና ዓላማ እንደሆነ አመላክተዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ክልሉ በጎማ በጀመረው ጥቅል ግዢ ሆኗል:: በቀጣይም ይህንኑ ወደ ሌሎች ግዢዎች በማስፋት የሃብት ብክነትን ለመቀነስና ጊዜና ወጪን ለመቆጠብ እየሰራ ነው:: በተለይም ውስን ጨረታዎችን በማስወገድ በግልጽ ጨረታ የጥቅል ግዢን ተግባራዊ በማድረግ ትልቅ ሥራ ተሰርቷል::



ዶክተር አራርሶ ገረመው

**ነጋዴዎቹ የንግድ ፈቃዳቸው የፌዴራልም ሆነ የክልሉ በክልሉ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ:: ማንኛውም የንግዱ ማህበረሰብ በየትኛውም ቦታ ሆኖ መሳተፍ ይችላል**

በዚህም የጎማ ግዢ ተሳክቶልናል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው መኪኖች እንደመኖራቸውና መኪና ደግሞ ትልቅ ሃብት እንደመሆኑ ጥቅል ግዢውን ተግባራዊ በማድረግ ብክነትን ማስወገድ ተችሏል ብለዋል:: በቀጣይም የኤሌክትሮኒክስና ሌሎች ግዢዎችን በማሕቀፍ ወይም በኤልክትሮኒክስ ግዢ በማድረግ ስኬታማ ለመሆን እየተሰራ ነው:: የፌዴራል መንግሥት እየተከተለ ያለው የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ወይም ኢጂፒን ተግባራዊ ለማድረግ ሲዳማ ክልል ግንባር ቀደም እንደሆነና አሁንም ሙሉ ለሙሉ ወደ ስርዓቱ ለመግባት እየተጠባበቀ እንደሆነ ተናግረዋል::

‹‹መንግሥት በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ እያደረገ ያለው የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ወይም ኢጅፒ ሌብነትን የሚያስቀር፣ ከሰው ንክኪ የጸዳ፣ ጊዜንና ጉልበትን በመቆጠብ ብክነትን የሚያስወግድ ነው›› ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ እነዚህን ችግሮች ለማስቀረት ሰፋፊ ሥራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ክልሉ የመንግሥት ግዢን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ለማድረግ መሄድ ያለበትን ርቀት ሄዷል:: ለዚህም በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ስልጠና ተሰጥቷል:: ስልጠና የተሰጣቸው አካላትም የኤሌክትሮኒክስ ግዢን ለመፈጸም ባሳዩት ፍላጎት መሰረት ከ300 የሚበልጡ ነጋዴዎች ተመዝግበዋል::

ነጋዴዎቹ የንግድ ፈቃዳቸው የፌዴራልም ሆነ የክልሉ በክልሉ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ:: ማንኛውም የንግዱ ማህበረሰብ በየትኛውም ቦታ ሆኖ መሳተፍ ይችላል:: ምክንያቱም፤ ኢጂፒ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ማለት በአንድ ክልል ብቻ ተወስኖ የመሸጥና የመግዛት ጉዳይ አይደለም:: ኬንያ፣ አውሮፓና አሜሪካም ሆኖ መወዳዳር ይቻላል:: ይህን ታሳቢ በማድረግ በአገሪቱ የትኛውም ክልል ሆኖ መወዳደር የሚችል ማንኛውም ነጋዴ መወዳደር ይችላል:: ይህም ርቀትን በማጥበብ፣ ጊዜን መቆጠብና ብክነትን በማስወገድ ረገድ ጉልህ ድርሻ አለው::

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ሀዋሳ ከተማ ላይ ትልቅ ፎረም መደረጉን ያስታወሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ቢሮው ከ300 ከሚልቁ የንግዱ ማህበረሰብ ጋር ሰፊ ውይይት አድርጓል፤ ስልጠናም ተሰጥቷል ብለዋል:: ቢሮው ለኤሌክትሮኒክስ ግዢ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ሰነዶችንና ናሙናዎችን በማሰባሰብ መመሪያዎችን ሰርቶ እንደጨረሰም ተናግረዋል:: የቅድመ ዝግጅት ሥራው ከዘጠኝ ወራት በላይ እንደወሰደ ጠቅሰው፣ ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ላይ ተግባራዊ መደረግ እንደነበረበትም አመላክተዋል:: ይህ እንዳይሆን የተለያዩ ውስጣዊና ውጪያዊ ችግሮች ያጋጠሟቸው መሆኑን ተናግረው፣ አሁን ችግሮች መፈታታቸውንና በቅርቡም ሙሉ ለሙሉ ወደ ግዢ ስርዓቱ እንደሚገባ አመላክተዋል::

የቢሮ ኃላፊው እንዳሉት፤ በዋናነት ኢጅፒን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ግዢን በኤሌክትሮኒክስ ለመፈጸም ትልቅ ሃብት ይጠይቃል:: የዳታ ማዕከል መገንባት ያስፈልጋል፤ ለዚህም ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለመስራት ስምምነት ተደርሷል::

እነዚህንና መሰል ግብዓቶችን ለማሟላት ትልቅ ገንዘብ የጠየቀ በመሆኑ ዝግጅቱ ብዙ ጊዜ ወስዷል:: ይሁንና በአሁኑ ወቅት ሀዋሳ ከተማ ፖሊ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ውስጥ የዳታ ማዕከል ኢንስቶል ማድረግ ተችሏል:: በቅርቡም አንድ ሰርቨር በማሟላት ኢጂፒን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው ዝግጅት ተጠናቋል:: ወደ ትግበራው ሲገባ የፋይናንስ ቢሮው ግዢውን በኤሌክትሮኒክስ ያደርጋል::

ከክልሉ ተቋማት መካከል ስምንቱ ለትግበራው መመረጣቸውን የቢሮ ኃላፊው ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል ከፍተኛ ሃብት የሚፈልጉት የትምህርት ቢሮ፣ ጤና ቢሮ፣ የፋይናንስ ቢሮ፣ ግብርና፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ መንገድና ትራንስፖርት፣ ውሃ እንዲሁም ሀዋሳ ከተማ ይገኙበታል:: እነዚህ ስምንት ተቋማት በተያዘው 2017 በጀት ዓመት ኢጅፒን ተግባራዊ ያደርጋሉ:: በቀጣይ በዞንና ወረዳ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል ብለዋል::

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ መሰረተ ልማት መሟላት እንዳለበት የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ በተለይም ወረዳኔት መዘርጋትና የኦንላይን ስርዓቱ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል:: በ2012 ዓ.ም ሲዳማ ዞን ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከኦንላይን ስርዓቱ ጋር መተዋወቅ እንደቻለ ገልጸው፣ በወቅቱ ከ15 ያልበለጡ ተቋማት የኦንላይን ስርዓትን መቀላቀላቸውን አስታውሰዋል:: አሁን ግን ከአራት ዓመት ወዲህ በተሰራ ሥራ ወረዳዎችን ጨምሮ 80 የሚደርሱ ተቋማት የኦንላይን ስርዓቱን መቀላቀል ችለዋል ይላሉ::

‹‹እነዚህ ሥራዎች ሲሰሩ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖልን አይደለም›› ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ አብዛኛው ሰው ከተለመደው ነገር ለመውጣት የሚቸገር በመሆኑ ቴክኖሎጂውን ለመላመድ ችግር ነበር:: እርግጥ ነው ቴክኖሎጂውን በመጠቀም ሥራን ማቅለል ይቻላል:: ይሁንና በማህበረሰቡ ዘንድ ለውጥን በቶሎ መቀበል አልተለመደም:: ስለዚህ ቀድሞ ከነበረው አካሄድ መውጣት የማይፈልጉ ብዙዎች ነበሩ::

ያም ሆኖ የመንግሥትን ግዢ በኢጅፕ መፈጸም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ አያጠራጥርም:: ኢጅፕ፤ 50 በመቶ በራሱ የኦዲት ሥራ የሚሰራ በመሆኑ ከኦዲት ሥራ ጋር ተያይዞ ያሉ ባለሙያዎች ሊያኮርፉ ይችላሉ:: ነገር ግን ባለሙያዎቹ ሥራ እንደማያጡና ራሳቸውን እንዲያሳድጉ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ::

ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሌብነትና ብክነትን መከላከል እንደሚቻል ያነሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ኢጅፕ ተግባራዊ የሚደረገው በዋናነት ወጪ ለመቀነስና ሃብት በአግባቡ እንዲመራ ነው ይላሉ:: ሃብቱ ደግሞ ለሕዝቡ ጤና፣ ትምህርት፣ መንገድና ለመሳሰሉት የሚውል በመሆኑ ይህንኑ አቅም እየገነባን ነው:: ሃብትን በአግባቡ ከመምራት ባለፈም ሌሎች ተጨማሪ ሃብቶች ሲገኙ በአግባቡ መምራት ከተቻለ ሃብት እየጨመረና ዕድገት እየተመዘገበ ይሄዳል ሲሉ ያብራራሉ::

‹‹አሁን የክልሉ ሕዝብ የሚፈልገው መልማት ነው:: በመሆኑም መንግሥት የክልሉን የመልማት ጥያቄ እንደየቅደም ተከተሉ እያስተናገደ ይገኛል›› ሲሉ ጠቅሰው፣ በዚህም በርካታ ውጤቶች መመዝገባቸውን አስታውቀዋል:: ሲዳማን ሞዴል የማድረግ ጉዞው መቀጠሉን ጠቅሰው፣ ሲዳማን ሞዴል እናደርጋለን ሲባልም በመልክና በቅርጽ ሳይሆን፤ በተለይም በክልሉ ሰላምና ጸጥታ ሰፍኖ ማህበረሰቡ በሰላም ተረጋግቶ መኖር እንዲችል ማድረግ አንዱ ነው ብለዋል:: ሌላው ንጽህና ያለው የግዢ ስርዓትና ንጽህና ያለው የሂሳብ አሰራርን በመፍጠር እንዲሁም ኢጅፕን በፍጥነት ተግባራዊ በማድረግ ሲዳማ ክልልን ሞዴል የማድረግ ጥረቱ መቀጠሉን አስታውቀዋል::

# ዓለም አቀፍ



## ብሊንከን ከጋዛው ጦርነት ወዲህ 11ኛ የመካከለኛው ምስራቅ ጉብኝታቸውን እያካሄዱ ነው

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን እስራኤል ገቡ፡፡ ሚኒስትሩ ለአንድ ሳምንት በሚዘልቀው የመካከለኛው ምስራቅ ጉብኝታቸው ወደ ዮርዳኖስና ኳታርም ያቀናሉ፡፡ ሚኒስትሩ ቴል አቪቭ የገቡት ሄዝቦላህ ወደ ማዕከላዊ እስራኤል በርካታ ሮኬቶችን ከተኮሰ ከሰአታት በኋላ ነው።

ብሊንከን የጋዛው ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ 11ኛ የመካከለኛው ምስራቅ ጉብኝታቸው ሲሆን፥ በእስራኤል ቆይታቸው ከጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁና ከመከላከያ ሚኒስትሩ ዮቭ ጋላንት ጋር ይመክራሉ። እስራኤል በጋዛ እና በሊባኖስ በኢራን ይደገፋሉ በሚባሉ ቡድኖች ላይ መጠነ ሰፊ ጥቃት እያደረሰች በምትገኝበት ወቅት የጀመሩት ጉብኝትም የተቋረጠውን የጋዛ ተኩስ አቁም ድርድር ማስጀመር ያለመ መሆኑን ተዘግቧል።

10 ጊዜ በእስራኤልና በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በመጓዝ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጥረት ያደረጉት ብሊንከን 11ኛው ጉዟቸውም የተሳካ ውጤት ይታይበታል ተብሎ አይጠበቅም። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተደጋጋሚና ያልተሳካ ጉዞም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ውድቀት ማሳያ ተደርጎ ሲነሳ ቆይቷል።

ከእስራኤል ባሻገር በዮርዳኖስ እና ኳታር ቆይታ የሚያደርጉት ዲፕሎማት በአሁኑ ጉዟቸው ግን ተጨባጭ ውጤት ያመጡ ዘንድ ይጠበቃል። ከሁለት ሳምንት በኋላ ከሚደረገው የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ አስቀድሞ በጋዛ የተኩስ አቁም ስምምነት ካልተደረሰ ለዴሞክራቷ ካማላ ሃሪስ ፈታኝ እንደሚሆን ነው ተንታኞች የሚያነሱት።

የጋዛውን ጦርነት ማስቆም ሳትችል በሊባኖስ ከሄዝቦላህ ጋር ውጊያ መጀመሩ የኔታንያሁ አስተዳደር ከ17 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወታደራዊ ድጋፍ ከፈቀደለት የባይደን መንግሥት ጋር ተደጋጋሚ ቅሬታ ውስጥ ገብቷል፡፡በቅርቡም እስራኤል በጋዛ ሠብዓዊ ድጋፍ እንዳይደርስ የምታደርገውን እገዳ በ30 ቀናት ውስጥ ካላቆመች ወታደራዊ ድጋፉ ሊቋረጥ እንደሚችል ብሊንከንና የመከላከያ ሚኒስትሩ ሊዩድ ኦስቲን በደብዳቤ ማሳሰባቸው የሚታወስ ነው ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

## የዛምቢያው ፕሬዚዳንት ለተቀናቃኛቸው ወስነው የነበሩ ሦስት ዳኞችን ከሥራ አባረሩ



የዛምቢያው ፕሬዚዳንት ሃኪዬንዳ ሂቺሌማ በዳኝነት ሥራቸው ላይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ፈጽመዋል ያሏቸውን የሀገሪቱን ሦስት ከፍተኛ ዳኞች ከሥራ አባረሩ። በፕሬዚዳንቱ የተሰናበቱት የሀገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ከስምንት ዓመት በፊት በተካሄደው እና የአሁኑ ፕሬዚዳንት በተሸነፉበት ምርጫ ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ውድቅ አድርገውት ነበር።

በተጨማሪም ዳኞቹ አሸናፊው ፕሬዚዳንት ኤድጋር ሉንጉ ለሁለት የምርጫ ዘመን በሥልጣን ላይ ከቆዩ በኋላ ለሦስተኛ ዙር እንዲወዳደሩ በተፈቀደበት አወዛጋቢ ውሳኔ ውስጥም ተሳትፈው ነበር። ዳኞቹ በፕሬዚዳንቱ ከመባረራቸው በፊት እገዳ ተጥሎባቸው የነበረ ሲሆን፣ ይኸው እገዳ እንዲነሳላቸው ለዳኞች ጉባዔ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መሆኑን ተከትሎ ነው።

ዳኞቹ ከሥራ የተባረሩት የሀገሪቱ የፍትህ ቅሬታዎችን የሚመለከተው ኮሚሽን "በአስቸኳይ እንዲሰናበቱ" ባቀረበው ሃሳብ መሠረት መሆኑን ከሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት የወጣው መግለጫ አመልክቷል። መግለጫው ጨምሮም "በዛምቢያ ሕገ መንግሥት መሠረት ዳኞችን የማሰናበት ሥልጣን ለፕሬዚዳንቱ የተሰጠ በመሆኑ" ውሳኔው መተላለፉን ገልጿል። በፕሬዚዳንቱ ከዳኝነት ሥራቸው የተሰናበቱት ሦስቱ የዛምቢያ ከፍተኛ ዳኞች በውሳኔው ላይ የሰጡት አስተያየት የለም።

የፍትህ ቅሬታዎችን የሚመለከተው ኮሚሽን ሦስቱ ዳኞች በተሰጣቸው ኃላፊነት አማካኝነት ተገቢ ያልሆኑ ከባድ ጥፋቶችን ፈጽመዋል በሚል በአንድ ግለሰብ የቀረበባቸውን ክስ ሲመርምር ቆይቷል። ባለፈው የአውሮፓውያን ዓመት ኮሚሽኑ ዳኞቹ ከስምንት ዓመት በፊት በተካሄደው ምርጫ ላይ ያሳለፉት ውሳኔ ተገቢ አልነበረም በሚል በአንድ ጠበቃ የቀረበለትን ክስ ውድቅ አድርጎት ነበረ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ምርጫ ለማስተናገድ እየተዘጋጀች ባለችው ዛምቢያ የወቅቱ ፕሬዚዳንት ሂቺሌማ እና ቀድሞው ፕሬዚዳንት ሉንጉ እንደሚፎካከሩ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በዚህም የተነሳ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ውጥረት እየጨመረ መሆኑ ይነገራል። የፕሬዚዳንቱ ውሳኔን በተመለከተ በሀገሪቱ ዜጎች መካከል የተደበላለቀ አስተያየት እየተሰጠ ነው።

ውሳኔው ሕጋዊ ነው ነገር ግን ፕሬዚዳንቱ እና ደጋፊዎቻቸው ለእራሳቸው በሚጠቅም መልኩ ርምጃ ወስደዋል ሲሉ የሀገሪቱን ፖለቲካ በቅርበት የሚከታተሉ ዜጎች ተችተዋል። ላውራ ሚቲ የተባሉ የፖለቲካ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ እንዳሉት "በ2016 (እአአ) የተካሄደውን ምርጫ በተመለከተ ዳኞቹ ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ አሳልፈዋል። ነገር ግን ፕሬዚዳንቱ የበቀል የሚመስል ውሳኔ መስጠታቸው በጣሙን አሳሳቢ ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

ነገር ግን የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጠበቃ የሆኑት ማኬቢ ዙሉ ርምጃውን "ሕገወጥ" በማለት "ሥራ አስፈጻሚው በፍትህ አካሉ ነጻነት ላይ ጣልቃ ለመግባት ያለመ ነው" ሲሉ ከሰው "የትኛውም ዳኛ ሕግ የመተርጎም ሥራውን በማከናወኑ ሊቀጣ አይገባም" ብለዋል።

በዛምቢያ ሕገ መንግሥት መሠረት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን ጨምሮ ሁሉም ዳኞች በሀገሪቱ የሕግ አገልግሎት ኮሚሽን ተመርጠው በፕሬዚዳንቱ ሚሾሙ ሲሆን፣ በሀገሪቱ ብሔራዊ ምክር ቤትም ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።




ብላቴና መጽሔት


ብላቴና የልጆች የሆነች፣ ስለልጆች የሚጻፍባት፣ ልጆችም ሃሳባቸውን የሚገልጹባት፣
ወላጆች ለልጆቻቸው በየወሩ በስጦታ የሚያበረክቷት የዚህ ዘመን ልጆች ገጸ በረከት ናት።

ብላቴና ከ3 ዓመት ጀምሮ ላሉ ልጆች እየተዝናኑ ቋምነገር እንዲጨብጡ በጥንቃቄ
እየተዘጋጀች በየወሩ ለህትመት የምትበቃ የልጆች መጽሔት፡፡

ብላቴናትን ይግዙ፣ ያንብቡ ለልጆችዎም ይስጡ።

ሰብስክራይብ በማድረግ ደንበኛ ይሁኑ!
በየወሩ በኪዮስኮቻችንና በጋዜጣ አዟሪዎች እጅ ያገኟታል፡፡

# ስፖርት



## "ኢትዮጵያ በ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት አቅም አላት"

- ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር )

ዓለማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት አቅም እንዳላት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከትናንት በስቲያ ምሽት ለካፍ ፣ለፊፋ ፕሬዚዳንቶች እና ለካፍ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከፍተኛ አመራሮች በታላቁ ቤተ-መንግሥት የእራት ግብዣ ባደረጉበት ወቅት ኢትዮጵያ የ2029 አፍሪካ ዋንጫን እንድታዘጋጅ በይፋ ጠይቀዋል። ለዚህም ኢትዮጵያ ትልቁን አህጉራዊ የእግር ኳስ መድረክ የማዘጋጀት አቅም አላት ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ እያስተናገደች ከምትገኘው 46ኛው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) መደበኛ ጉባዔ አስቀድሞ የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሞትሴፔን እና የካፍ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከፍተኛ አመራሮችን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ያነጋገሩ ሲሆን፣ በመጠናቀቅ ላይ ያለውን የብሔራዊ ስታዲየም ግንባታንም በጋራ መጎብኘታቸውን ገልፀዋል። ኢትዮጵያ ይህ ጠቃሚ ጉባዔ የተሳካ እንዲሆን ለማገዝ በሚገባ መዘጋጀቷንም ተናግረዋል።

የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙትሴፔ(ዶ/ር) በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበል ምስጋና አቅርበው፣ የኢትዮጵያውያን ባህል፣ እሴትና እንግዳ ተቀባይነት "ኢትዮጵያ ቤታችን እንደሆነች እንዲሰማን አድርጎናል" በማለት ተናግረዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ አክለውም ኢትዮጵያ የ2029ኙን የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት ያቀረበችውን ጥያቄ ካፍ ከኮሚቴው ጋር እንደሚመክርበት ገልጸዋል።

የፊፋ ፕሬዚዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖም "የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ የኛም ሀገር ነች" ሲሉ ተናግረዋል። በመርሐ ግብሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለሁለቱም ፕሬዚዳንቶች የኢትዮጵያ እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን ማሊያን በስጦታ አበርክተዋል፡፡ በተመሳሳይ የፊፋው ፕሬዚዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ 2029 የሚል ፊርማቸውን ያሳረፉበትን ኳስ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አበርክተዋል።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለሁለቱም ፕሬዚዳንቶች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን ማሊያ በስጦታ አበርክተዋል፣

በተመሳሳይ እለት ቀን ላይ በአዲስ አበባ ስቴድየም በተካሄደ የወዳጅነት ጨዋታ መርሃግብር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ሳላዲን ሰዒድ፣ አዳነ ግርማና ሌሎችም የቀድሞ የዋልያዎቹ ኮከቦች ስብስብ ከቀድሞ የተለያዩ ሀገራት የአፍሪካ ኮከቦች ጋር የወዳጅነት ጨዋታ አድርገዋል። የካሜሮን ኮኮብ ተጫዋች ሳሙኤል ኢቶ፣ የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪ ሞትሴፔ፣ የቀድሞው ካሜሩናዊ ኮከብና የአሁኑ የሀገሩ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ኢቶ፣ ናይጄሪያዊው የቀድሞ ኮከብ ጄይጄይ አካቻና ሌሎችም የወዳጅነት ጨዋታው ተካፋይ ሆነዋል።

ይህንን በተመለከተ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ 46ኛው የካፍ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሁም ጉባዔውን በማስመልከት የተካሄደው የወዳጅነት ጨዋታ የእግር ኳስ ቤተሰቡን ያነቃቃ እንዲሁም የኢትዮጵያን ገፅታ የገነባ መሆኑን ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ አያይዘውም፣ 46ኛው የካፍ ጠቅላላ ጉባዔ ዝግጅትን እንዲሁም የኢትዮጵያን የ2029 አፍሪካ ዋንጫ የማዘጋጀት ፍላጎትን እንዳላት ገልጸው መንግሥትም በሀገሪቷ የሚገኙ ግንባታቸው የተጀመሩ ስታዲየሞችን የማጠናቀቅ ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

"የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ የማጠናቅ ልምድ ያለን በመሆኑ በግንባታ ላይ ያሉ ስታዲየሞችን የማጠናቀቅ ብቃትም ተነሳሽነትም አለን" ያሉት ሚኒስትሯ፣ አብዛኞቹ ስታዲየሞች በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን አስታውሰው፤ የአፍሪካ የእግር ኳስ የበላይ አካል (ካፍ) ይሁንታውን የሚሰጥ ከሆነ ከሚኖረው 5 ዓመት አስቀድሞ ስታዲየሞቹን የማጠናቀቅ ሥራ እንደሚሠራ አሳውቀዋል። ለሥራዎቹ ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት እና ብቃትም እንዳለ አስረድተዋል።

ከስቴዲየሞቹ ባሻገርም ተተኪ ስፖርተኞች የሚወጡባቸው ትንንሽ ሜዳዎች (Mini stadium) ታሳቢ እንደሚደረጉ እና ውድድርን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የመሠረተ ልማቶች ሥራዎች ላይ ትኩረት እንደሚደረግም ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴም ካፍ ትናንት ጠቅላላ ጉባዔውን ሲጀምር በመድኩ ተገኝተው ካፍ የኢትዮጵያን የአፍሪካ ዋንጫ የማስተናገድ ጥያቄ ተቀብሎ እንዲያጸድቅ ጥሪ አቅርበዋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ እግር ኳስ ትልቅ ዐሻራ እንዳላትና እ.አ.አ በ1957 ካፍ ሲመሠረትም መሥራች ከነበሩ ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗን በማስታወስ፣ የካፍ ፕሬዚዳንት የነበሩት ይድነቃቸው ተሰማ የአፍሪካ እግር ኳስ በዓለም መድረክ የሚገባውን ቦታ እንዲያገኝ የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

‹‹ኢትዮጵያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እግር ኳስ ወዳጆች ያሉባት ሀገር ናት›› ያሉት ፕሬዚዳንት ታዬ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ እግር ኳስ ያላትን ታሪካዊ ድርሻ ከግምት በማስገባት በ2029 የሚካሄደውን የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት ጥያቄ ማቅረቧን ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫውን ተጠቅማ የአፍሪካን እግር ኳስ ለማሳደግና በስፖርቱ ሀገር ለመገንባት እንደምትሠራም አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ስታዲየሞች እየገነባችና ያሉትንም ማሻሻያ እያደረገች እንደምትገኝም አመልክተዋል።

## ከነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## አዲሱ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያ

ኃይለማርያም ወንድሙ

### የማሻሻያው መነስኤ

የሀገር በቀል ሪፎርም የኤሌክትሪክ ኃይል ዘርፉን በጥልቀት በመዳሰስ በዘርፉ ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን ለይቶ አስቀምጧል:: ሪፎርሙ በችግርነት ከለያቸው ጉዳዮች መካከል ዝቅተኛ የሆነ የሀገር ውስጥ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ፣ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽነትና የማመንጨት አቅም፣ አስተማማኝ ያልሆነ የኃይል አቅርቦት፣ ዘላቂነት የጎደለው የኢንቨስትመንትና ያልተቀላጠፈ አሠራር ይጠቀሳሉ:: ለችግሮቹም የለውጥ ርምጃዎችን በማመላከት ወደ ትግበራ ከገባ ሰነባብቷል::

በተወሰዱት የለውጥ ርምጃዎችም በዘርፉ ለዘመናት የተከማቸውን እዳ በተወሰነ ደረጃ ወደ ሌላ ተቋም በማዘዋወር የዘርፉን ዕዳ የማቃለል፤ ሳይከለስ የቆየውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ክፍያን በማስተካከልና እንዲተገበር በመወሰኑ ዘርፉ የተሻለ ገጽታ እንዲኖረው አስችሏል::

ይሁን እንጂ ዘርፉ ለሥራ የሚያውላቸውን ግብዓቶች ከውጪ ገበያ የሚያገኝ እንደመሆኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የዋጋ ንረት ፈተና ብሎም በየጊዜው በምንዛሪ ላይ የተደረገው ለውጥና የዋጋ ግሽበት አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረውበታል:: በመሆኑም በጥናት ላይ የተመሠረተ የዋጋ ማስተካከያ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊና ወቅቱም የጠበቀ ጉዳይ ሆኗል::

በመሆኑም ዘርፉ የሚመራበት የታሪፍ አዘገጃጀትና ማስወሰኛ መመሪያ መሠረት በሁለቱ ተቋማት /የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት/ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ክፍያ መጠን ጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል:: ሰነዱ በነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ተገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥት እንደቀረበ ባለሥልጣኑ ያወጣው የብሔራዊ ግሪድ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ክፍያ የውሳኔ ምክረ ሃሳብ ሰነድ ያስረዳል::

የብሔራዊ ግሪድ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ክፍያ የውሳኔ ምክረ ሃሳብ ሰነድ እንደሚያስረዳው በሥራ ላይ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ሽያጭ ታሪፍ የቆይታ ጊዜው ታህሳስ 2015 ዓ.ም ላይ ያበቃ ነው:: በመሆኑም አገልግሎት አቅራቢዎቹ ኤሌክትሪክን ለሕዝብ የሚያቀርቡበት የመሸጫ ተመንን ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ወጪያቸውን ለመመለስ በሚያስችል ወቅታዊ የታሪፍ ተመን በውጭ አማካሪ ድርጅት አማካይነት አስጠንተዋል ባለሥልጣኑም በተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 521 መሠረት በማድረግ የታሪፍ ጥናቱ በመገምገም ለመንግሥት የውሳኔ ምክረ ሃሳብ አቅርቧል::

የታሪፍ ጥናት ሰነዱን በመገምገም የውሳኔ ምክረ ሃሳቡን ለማቅረብ መነሻ ምክንያቶች አሉት:: የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሀሴ 26 ቀን 2010 ዓ/ም ባሳለፈው ውሳኔ ከታህሳስ 2011 ዓ/ም ጀምሮ ለ4 ዓመታት የሚጸና የታሪፍ ጊዜ በማብቃቱ፣ ኤሌክትሪክ ዋነኛ የኃይል ምንጭ በመሆኑ የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ከማንቀሳቀስ አንፃር ያለውን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት ዘርፉ ወጪውን እየሸፈነ ለቀጣይ ኢንቨስትመንትና የአገልግሎት መሻሻል አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችል እና በአዲስ መልክ ተጠንቶ የቀረበው የኤሌክትሪክ ታሪፍ የሸማቹን አቅም ያገናዘበ እና የኢንቨስትመንት ፍሰትን የማይጎዳ እንዲሆን ለማስቻል እንደሆነ ሰነዱ ያስረዳል::

በኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ላይ የተደረገው ማስተካከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰኔ 13/2016 ዓ.ም መጽደቁ ይታወሳል። ይህ ተከትሎ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የታሪፍ ማሻሻያው ከመስከረም 1 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ሆኗል:: የታሪፍ ማስተካከያው የደንበኞችን የኃይል አጠቃቀም መሠረት ያደረገ ነው።

በዚህም መሠረት የቤት ደንበኞች፣ የንግድ ተቋማት፣ ዝቅተኛ ኢንዱስትሪ፣ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲሁም የመንገድ መብራት ተጠቃሚዎች በሚል ተከፋፍሏል። የቤት መብራት ተጠቃሚዎችን በተመለከተ "እንደ አጠቃቀማቸው አሁን ከሚከፍሉት እና ጭማሪ ከተደረገበት መካከል ያለውን ልዩነት ሲከፍሉ እንደ አጠቃቀማቸው ድጎማ ተደርጓል"።

### ድጎማው ምን ይመስላል ?

- 50kW በታች ለሚጠቀሙ ደንበኞች ያለውን ልዩነት 75 በመቶ የሚሆነውን ይደጎማሉ፤
- ከ50kW - 100KW ለሚጠቀሙ ደንበኞች ያለውን ልዩነት 40 በመቶ የሚሆነውን ይደጎማሉ፤
- 200kW - 300 Kw ለሚጠቀሙ ደንበኞች ያለውን ልዩነት 4 በመቶ የሚሆነውን ይደጎማሉ፤
- 400kW - 500 KW የሚሆነውን ማሻሻያውን ያለምንም ድጎማ ይከፍላሉ
- ከ500kW በላይ የሚሆነውን ደግሞ ሌላውን ተጠቃሚ የሚደግፉበት የጎንዮሽ ድጎማ ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል።

### የአከፋፈሉ ሁኔታ ምን ይመስላል ?

የተደረገው የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻያው (የተጨመረው 6 ብር) የሚከፈለው ከመስከረም 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ጊዜ ሳይሆን በ16 ዙር በሚደረግ የሂሳብ ማስተካከያ በአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚተገበር ነው። ይህም ማለት በዓመት 4 ጊዜ በ4 ዓመት ደግሞ 16 ጊዜ የሚተገበር የሂሳብ ማስተካከያ የያዘ ነው።

ይህ የታሪፍ ማሻሻያ በዋነኛነት የወጣበትን ወጪ ለመሸፈን (A cost reflective tariff) መሠረት ያደረገ ነው:: ከአራት ዓመታት በኋላ ደግሞ [በ16 ዙሮች በሚደረግ ማስተካከያ] 1 ነጥብ 56 ብር መክፈል ይጀመራል:: የክፍያ ታሪፉ ከኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ያለው ጫና ላይ ጥናት ያደረገ ነው:: ይህም ከአራት ዓመት በኋላ የሚኖረው ተጽዕኖ 2 በመቶ ብቻ እንደሆነ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የተገኘ መረጃ ይገልፃል::

የታሪፍ ማሻሻያው ሊፈጥረው የሚችለውን ጫና ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከሁለቱም ተቋማት ጋር ማለትም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በመቀናጀት ሠርቷል:: በተደረገው ጥናት የ100 ፐርሰንት ታሪፍ ጭማሪ ቢደረግ እንኳን በሀገር ደረጃ የሚፈጠረው የዋጋ ንረት አነስተኛ መሆኑ ታምኖበታል:: ለትግበራ በቀረበው የታሪፍ ውሳኔ ሃሳብ ላይ ግን ታሪፉ ከ100 ፐርሰንት ባነሰ ምጣኔ እንዲተገበር ተደርጓል::

በመኖሪያ ቤት የታሪፍ ምድብ ሥር የሚገኙት ከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚዎች ዝቅተኛ የሆኑትን የኃይል ተጠቃሚዎች የሚደጉሙበት አሠራር መዘርጋቱን የብሔራዊ ግሪድ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ታሪፍ ክፍያ የውሳኔ ምክረ ሃሳብ ሰነድ ያስረዳል።